# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ማክሰኞ

82ኛ ዓመት ቁጥር 129 ጥር 9 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ

pepsi




## “ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የኢንዱስትሪ ኢኮኖሚ ሽግግርን በማሳለጥ ላይ ትገኛለች”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር)

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ኢኮኖሚ ሽግግርን በማሳለጥ ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገትን ለማስፈን እየተገበረች የምትገኘው እቅድ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶክተር) በዘላቂ የኢኮኖሚ ዕድገት እና በአየር ንብረት ለውጥ ላይ በሚመክረው 15ኛው የአቡዳቢ አለም አቀፍ «ሰስቴኔቢሊቲ»ጉባኤ ላይ ባስተላለፉት መልእክት፤ በአፍሪካ ከሚገኙ አገራት በፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ላይ የምትገኘው ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር ኢኮኖሚን እየገነባች ትገኛለች ብለዋል። ዘላቂነት ያለው የ10 ዓመታት


“ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## ተገቢውን የባንክ አገልግሎት እያገኘን ባለመሆኑ ተቸግረናል

- የዱብቲና የመተማ ነዋሪዎች

## ችግሩ የተፈጠረው ብሔራዊ ባንክ በዓፈው ደብዳቤ ምክንያት ነው

- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በባንክ የቆጠቡትን ገንዘብ ሂሳብ ከከፈቱበት ቅርንጫፍ ውጪ ማውጣት እንዳልቻሉና ከሌሎች አካባቢዎች የሚላክላቸው ገንዘብ ወደ ባንክ ሂሳባቸው መግባት ባለመቻሉ መቸገራቸውን የዱብቲና መተማ ነዋሪዎች ገለጹ። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በበኩሉ በተጠቀሱት አካባቢዎች ችግሩ የተፈጠረው ብሔራዊ ባንክ ባስተላለፈው ደብዳቤ መሆኑን ገልጿል።

የአፋር ብሔራዊ ክልል የዱብቲ ወረዳ ነዋሪ መሀመድ ሀሰን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዱብቲ ከተማ በሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የረጅም ጊዜ ደንበኛ ቢሆኑም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተገቢውን የባንክ አገልግሎት ለማግኘት ተቸግረዋል።


ተገቢውን የባንክ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ
NATIONAL BANK OF ETHIOPIA
ADDIS ABABA



## በጦርነቱ የተጎዳው ኢኮኖሚ መልሶ እንዲያገግም ለመሰረተ ልማት ግንባታና ጥገና ትኩረት መስጠት ይገባል

- ዶክተር ጉቱ ቴሶ
ምጣኔ ሀብት ባለሙያ

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- በጦርነቱ የተጎዳው ኢኮኖሚ በፍጥነት እንዲያገግም ከሰላም ቀጥሎ ለኢኮኖሚው ዘርፍ አጋዥ የሆኑ መሰረተ ልማቶች ግንባታ እና ጥገና ትኩረት መስጠት እንደሚገባ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ገለጹ።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያ ዶክተር ጉቱ ቴሶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሰላም ለኢኮኖሚ እድገት


በጦርነቱ የተጎዳው ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## አምባሳደሮች ለኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ልዩ ትኩረት መስጠታቸውን ገለጹ


ገጽ 4









## የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃን ማሰራጨት ስለሚያስከትለው ተጠያቂነት የኅብረተሰቡን ግንዛቤ ማዳበር ይገባል


ገጽ 3



ዶክተር ፍስሐ አሰፋ

## የጎርጎራ ፕሮጀክት የማጠናቀቂያ ምዕራፍ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- የገበታ ለሀገር ፕሮግራም አካል የሆነው የጎርጎራ ፕሮጀክት የማጠናቀቂያ ምዕራፍ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን የፕሮጀክቱ ስራ አስኪያጅ ዶክተር ፍስሐ አሰፋ ገለፁ።

በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሃሳብ አመንጪነት ከሚከናወኑ የገበታ ለአገር ፕሮጀክቶች መካከል የጎርጎራ ፕሮጀክት አንዱ መሆኑ ይታወቃል።

የጎርጎራ ፕሮጀክት በተለይም የሰሜን ኢትዮጵያን የቱሪዝም መዳረሻነት ይበልጥ በማስፋትና በማጠናከር ጉልህ ፋይዳ ይኖረዋል የተባለ አገራዊ የልማት ፕሮጀክት ነው።

የፕሮጀክቱን አጠቃላይ ክንውን እና አሁን ያለበትን ደረጃ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎች፣ የሚሲዮን መሪዎችና የተጠሪ ተቋማት የሥራ ኃላፊዎች በስፍራው በመገኘት ጎብኝተዋል።

የፕሮጀክቱን በጥራትና በፍጥነት መከናወን ያደነቁት አምባሳደሮቹ ለኢትዮጵያ የቱሪዝም እድገት ወደ ፊት መራመድ የሚችል ቋሚ ቅርስ መሆኑንም ተናግረዋል።

የጎርጎራ ፕሮጀክት ስራ አስኪያጅ ዶክተር ፍስሐ አሰፋ፤ የፕሮጀክቱ ክንውን በጥራትና በፍጥነት በጥሩ ሁኔታ እየተከናወነ መሆኑን ገልጸዋል።

በጣና ሐይቅ ላይ የተገነባውን አንፊ ቴአትር ጨምሮ ሬስቶራንቶች፣ ወደብ እና ሌሎች አገልግሎት መስጫ ግንባታዎች መጠናቀቃቸውንም አብራርተዋል።

የፕሮጀክቱ አካል የሆነው የመንገድ ግንባታ መጠናቀቁን ጠቅሰው፤ ቀሪ የግንባታ ስራዎችም የማጠናቀቂያ ምዕራፍ ላይ ይገኛሉ ነው ያሉት።

የማጠናቀቂያ የግንባታ ስራዎች በአጭር ጊዜ የሚከናወኑ መሆኑን ጠቁመው፤ አጠቃላይ ስራውን በሶስት ወራት ውስጥ አጠናቆ ለማስረከብ ሌት ከቀን እየተሰራ ነው ብለዋል።

የጎርጎራ ፕሮጀክት ሲጠናቀቅ ዘመናዊ ግንባታ ታክሎበት በማራኪ ገጽታና የመልክአ ምድር አቀማመጡ በኢትዮጵያ አስደናቂ ከሚባሉ ስፍራዎች መካከል አንዱ እንደሚሆን ስራ አስኪያጁ ተናግረዋል።

በጣና ሐይቅ ምዕራባዊ ዳርቻ የሚገኘው ጎርጎራ፣ በደቡብ ምዕራብ ሸዋ የሚገኘው ወንጪ እና በኮንታ የሚገኘው ኮይሻ የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች መሆናቸው ይታወቃል ሲል ኢዜአ ዘግቧል።

# የበጋው ደረቃማ የአየር ሁኔታ በሚቀጥሉት አሥር ቀናትም ቀጣይነት ይኖረዋል

በሪሁ አረጋ

አዲስ አበባ፡- በሀገራችን አብዛኛዎቹ አካባቢዎች የበጋው ደረቃማ የአየር ሁኔታ በሚቀጥሉት አሥር ቀናትም ቀጣይነት እንደሚኖረው ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ፡፡

የኢንስቲትዩቱ የሜቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ምክር አገልግሎት እና ምርምር ዘርፍ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አሳምነው ተሾመ ገሜ(ዶ/ር) እንደገለጹት፣ በሀገራችን ያለው የበጋው ደረቃማ የአየር ሁኔታ በሚቀጥሉት አሥር ቀናትም ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡

በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ተፋሰስ አካባቢዎች ላይም የበጋው ደረቃማ የአየር ጠባይ የሚስተዋል ይሆናል ያሉት ዳይሬክተሩ፣ ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት የሚያገኙባቸው ቀናት እንደሚሆኑ ጠቁመዋል፡:

በአስር ቀናትም በመደበኛ ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ጠባይ አመዝኖ እንደሚቆይ የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፣ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በአንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን እንደሚኖርም ገልጸዋል፡፡

አያይዘውም በሰሜን ምሥራቅ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ በጥቂት ሥፍራዎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ ሲሉ ተናግረዋል።

በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ እየታየ ያለው የበጋው ደረቃማ የአየር ሁኔታ በሚቀጥሉት አሥር ቀናትም ቀጣይነት እንደሚኖረው የሚጠበቅ ነው፡፡ በተለይም በደጋማው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጣይነት ይኖረዋል ብለዋል፡፡

አልፎ አልፎ በሚጠናከሩ ዝናብ ሰጪ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ምክንያት በሰሜን ምስራቅ በሰሜን ምዕራብ እንዲሁም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን የሚኖራቸው ይሆናል ያሉት ዳይሬክተሩ፤ ከዚህ ጋር በተያያዘም አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ሊኖራቸው ይችላል ብለዋል፡፡

ይህም ከአማራ የሰሜንና የደቡብ ወሎ ዞኖች ሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም ዞኖች፤ የአፋር ዞን 2 እና 4፣ የመካከለኛውና ምዕራብ ትግራይ ዞኖች ከኦሮሚያ ጅማ፣ ኢሉ አባቦራ፣ ምዕራብና ምስራቅ ወለጋ እና ሆሮ ጉድሩ፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልል የቤንች ማጂ ዞን እንዲሁም ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል የሸካ እና ከፋ ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች ደረቅ ሆነው ይቆያሉ ብለዋል፡፡

ሁኔታው በእርሻ ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ በመደበኛ ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የመኸር ሰብል አብቃይ አካባቢዎች ላይ የድህረ-ሰብል ስብሰባ ተግባራት በስፋት የሚከናወኑበት ወቅት መሆኑን ያወሱት ዳይሬክተሩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ የበልግ ተጠቃሚ አካባቢዎች መጠነኛ እርጥበት ሊያገኙ የሚችሉበት ነው ብለዋል።

በሀገራችን ቀደም ብለው የተሰበሰቡ ሰብሎችን ለመውቃትና በተዘጋጀላቸው ስፍራ ለማከማቸትም ሆነ ወደገበያ ለማውጣት የሚያስችል በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በድህረ-ሰብል ስብሰባ ስራዎች የምርት ብክነት እንዳይኖር አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ እንዲያከናውኑ መክረዋል።

እንደ ዳይሬክተሩ ገለጻ፣ ከሚጠበቀው ደረቃማ የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ በደጋማ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት እንደሚኖረው የሚጠበቅ ነው፡፡

ቅዝቃዜውን የመቋቋም አቅማቸው ዝቅተኛ በሆኑና በመስኖ በሚለሙ የፍራፍሬ ተክሎች፣ በጓሮ አትክልቶችና በቋሚ ተክሎች እድገትም በአንዳንድ የቤት እንስሳት ላይ የተወሰነ አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል።

በመሆኑም በዘርፉ ለተሰማሩ አርሶ አደሮችና ለሚመለከታቸው አካላት የአካባቢን ሙቀት ሊጨምሩ የሚችሉ ዘዴዎችን በመጠቀም በቅዝቃዜ ምክንያት ሊከሰት የሚችለውን አሉታዊ ተጽዕኖ ለመቀነስ የሚያስችሉ ስራዎችን ሊያከናውኑ ይገባል ብለዋል፡፡

በሰሜን ምሥራቅ፣ በምዕራብና በደቡብ ምዕራብ ጥቂት ሥፍራዎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው የእርጥበት መሻሻል ሊኖር እንደሚችል የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፣ ሁኔታው የአፈር ውስጥ እርጥበት እንዲሻሻልና የበልግ ወቅት እርሻን አስቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማድረግ አወንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ ሁኔታውን በመረዳት ከወዲሁ ዝግጅት እንዲያደርጉ ጠቁመዋል።

በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ በመደበኛ ሁኔታ በአብዛኛዎቹ ተፋሰስ አካባቢዎች ላይ የበጋው ደረቅ የአየር ጠባይ እንደሚስተዋል የጠቆሙት ዳይሬክተሩ፣ ከበልግ ወቅት መቃረብ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የበልግ እርጥበት ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት የሚያገኙበትም ነው ሲሉ ተናግረዋል።

በተወሰኑ ተፋሰሶች ላይ ከዝቅተኛ እስከ መካከለኛ የእርጥበት ሁኔታ ይኖራቸዋል ሲሉ የተናገሩት ዳይሬክተሩ፣ በላይኛው እና የመካከለኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ የመካከለኛው እና የታችኛው አሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ እና በጥቂት የላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች እንደሚገኙበት አመላክተዋል፡፡ በተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች በደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ ስር እንደሚቆዩ ይጠበቃል ብለዋል።

የአየር ሁኔታው በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ባሳለፍናቸው የጃንዋሪ የመጀመሪያው አስር ቀናት በአብኛዎቹ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ አመዝኖባቸው የቆየ ነበር፤ በመጀመሪያዎቹ ቀናት በጥቂት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ በመካከለኛው አዋሽ፣ በጥቂት የላይኛው ዋቢ ሸበሌ እና ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት እንደሚኖራቸው የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

# 1 ነጥብ 2 ቢሊየን ብር ወጪ የተደረገባቸው ማሽነሪዎች ለኢንተርፕራይዞች ተሳልፈዋል

## - ለ17 ሺ ዜጎች የስራ ዕድል ተፈጥሯል

ሞገስ ተስፋ

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት አመታት አንድ ነጥብ ሁለት ቢሊየን ብር የሚያወጡ ማሽናሪዎች አራት ሺ 500 ለሚሆኑ ኢንተርፕራይዞች ማስተላለፍ መቻሉን የአዲስ የካፒታል እቃ ፋናንስ ማህበር አስታወቀ፡፡ ለ17 ሺ ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡

የአዲስ የካፒታል እቃ ፋይናንስ ንግድ ስራ አክስዮን ማህበር ዋና ስራ አስኪያጅ አቶ መሳይ እንሴኔ እንደገለጹት፤ የኢንተርፕራይዝ ልማትና የካፒታል እቃ ፋይናንስ አገልግሎት የካፒታል እቃ ፋይናንስ ሊዝ ለኢንተርፕራዝ ልማት መሳሪያ በመሆን ለምርታማነት ዕድገት ወሳኝ ሚና እየተጫወተ ነው፡፡ ኢንተርፕራይዝ ልማት በዋናነት የሚደራጅበት አንድ ግብዓት የሚሆነው የካፒታል እቃ ፋይናንስ ነው፡፡

የካፒታል እቃ ፋይናንስ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰፊ አስተዋጽኦ ያለውና ብዙ አገራት ተፈላጊ አገልግሎት ዘርፍና ከፋይናንስ ዘርፉ አንዱ መሆኑን የገለጹት ስራ አስኪያጁ፤ ዘርፉ ከባንክ፣ከማይክሮ ፋይናንስ፣ ኢንሹራንስ በመቀጠል አራተኛው የፋይናንስ ዘርፍ ነው፡፡ ስለዚህ የሊዝ ፋይናንስ ተቋማት በኢንተርፕራዝ ልማት ላይ ያላቸው ሚና የጎላ ነው ብለዋል፡፡

እንደ አቶ መሳይ ገለጻ፤ የካፒታል እቃ ሊዝ ፋይናንስ በኢትዮጵያ ስራ ከጀመረ ስድስት አመቱ ነው ኢንተርፕራይዞች ስልጠና ወስደው፣ ቦታ አዘጋጅተው፣ ክህሎታቸውን አዳብረው ባሉበት ደረጃ ትልቅ አቅም የሚሆነው የካፒታል እቃ ፋይናንስ ነው፡፡ ፋይናንሱ የዋስትና ችግር የሚፈታ የሚፈልጉትን የማሽን አይነት ሊያቀርብ የሚችል ነው፡፡ መንግስት ሊሸፍናቸው የሚችላቸው ጥቅማጥቅም ያሉት ከታክስ ተያይዞ የሚመጡ ቀረጦችን ኃላፊነቱን ወስዶ ሊሰራ የሚችልበት አሰራር የሊዝ ፋይናንስ በመሆኑ ኢንተርፕራይዞች ወደ አምራችነት የሚሸጋገሩበት ሁኔታ ቀላል ነው፡፡



አቶ መሳይ እንሴኔ

ያለ ካፒታል እቃ ፋይናንስ አቅርቦት ኢንተርፕራይዝ ልማት ያስቸግራል ያሉት ስራ አስኪያጁ፤ በካፒታል እቃ ፋይናንስ ጥሩ ደረጃና ልምድ ያላቸው አገሮች አውሮፓና ምስራቁ አገራት ተጠቃሽ ናቸው፡፡ በአፍሪካ ደረጃም የምዕራብ አፍሪካ አገራት አብዛኛዎቹ ይህን አሰራር በመጠቀም እድገት እያስመዘገቡ ነው ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያም አዋጁን ከማሻሻል ጀምሮ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች መነሻ ካፒታል 200 ሚሊየን ብር በመፍቀድ የተጀመረው ስራ ትልቅ ነው፡፡ አዲስ የሊዝና ፋይናንስ ማህበር ከዚህ በፊት ከነበረው ስራ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ አዲስ አበባ ላይ በስራ ዕድል ፈጠራ፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር በተጨባጭ የሚታይ ለውጥ እንዲመጣ አድርጓል፡፡ አገር ውስጥ ገብተው የማያውቁ ማሽነሪዎች ገብተው እንዲሰሩ መደረጉን አቶ መሳይ ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ መሳይ ገለጻ ከሆነ፤ በተቋም ደረጃ እስካሁን አንድ ነጥብ ሁለት ቢሊየን ብር የሚያወጡ ማሽናሪዎች 18 ሺ አባላት ላሉት አራት ሺ 500 ለሚሆኑ ኢንተርፕራይዞች ተላልፏል፡፡ በዚህም ለ 17 ሺ ዜጎች የስራ ዕድል መፍጠር ተችሏል፡፡ አሁን ላይ ከዩኒቨርሲቲ ተመርቆ ብዙም የመንግስት ስራ ፍለጋ ከመዞር ይልቅ በዘርፉ ተሰማርቶ የመቀየር ፍላጎታቸው እያደገ ነው፡፡

ኢንተርፕራይዞች ስራ ለመጀመር የሚያስችላቸውን የቦታ፣ የንግድ ፈቃድ ካሟሉ በኋላ በማኑፋክቸሪንግ 15 በመቶና ለአገልግሎት ዘርፍ 25 በመቶ የቅድመ ክፍያ ማዘጋጀት ነው፡፡ ቅድመ ክፍያው የማሽኑ ባለቤትነት እሳቤ እንዲኖር ለማድረግ ሲሆን ሰርተው መክፈል የሚችሉበት መሆኑን ስራ አስኪያጁ ተናግረዋል፡፡

ብዙዎች ኢንተርፕራይዞች የፋይናንስ እቃ አገልግሎት መኖሩን አያውቁትም፡፡ ይህን በመገንዘብ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በመሆን ውጤታማ መሆን የሚችሉበትን እድል እንዲጠቀሙ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ዜና

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት
ETHIOPIAN DIASPORA SERVICE

## ዳያስፖራዎች ለ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች የቴክኖሎጂ ስልጠና መስጠት ጀመሩ

**ሙሳ ሙሐመድ**

አዲስ አበባ፡- ዳያስፖራዎች በውጭ ሀገራት ሲኖሩ ያካበቱትን የቴክኖሎጂ ዕውቀትና ክህሎት ለማሸጋገር ያለመ ስልጠና ከመላ ሀገሪቱ ለተወጣጡ የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎች መስጠት ጀመሩ።

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎት የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር አቶ ወንደሰን ግርማ በስልጠናው ማስጀመሪያ መርሃግብር ላይ እንዳስታወቁት፤ ዳያስፖራዎች የሚሰጡት ስልጠና በአዲስ አበባ የተመረጡ አራት ትምህርት ቤቶች ለሶስት ሳምንታት የሚቆይ ነው፡፡

ዳያስፖራዎች ለተማሪዎች ልምዳቸውና ክህሎታቸውን በቅርበት በሚያስተላልፉበት መድረክ "ብሩህ ትውልድ" የተሰኘ የኮምፒውተር ፕሮግራሚንግ ስልጠና ይሰጣል ሲሉ አስታውቀዋል።

አቶ ወንደሰን እንደገለጹት፤ ስልጠናው ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ዳያስፖራዎች ለዘመናት በውጭ ሀገራት ሲኖሩ ያካበቱትን የቴክኖሎጂ ዕውቀትና ክህሎት ወደ ሀገር ቤት የሚያሸጋግር አንድ አካል ነው።

ጌት ፋክት ኢትዮጵያ የተሰኘው ተቋም ስልጠናው ላይ የሚሳተፉ ዳያስፖራዎችን በአሜሪካ ኤም አይ ቲ ዩኒቨርሲቲ በማስተባበር እንዳስመጣቸው ገልጸዋል።

ከመላው ኢትዮጵያ የተወጣጡ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች በኮምፒውተርና ተዛማጅ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ክህሎት እንዲያዳብሩ የሚረዳ ዕውቀት ያገኛሉ። በቀጣይ ስልጠናውን በማስፋት በተለያዩ አካባቢዎችና ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ለማቅረብ ጥረት ይደረጋል ብለዋል።

በአሜሪካ የጌት ፋክት ኢትዮጵያ ተቋም መስራች ከሆኑት መካከል ዶክተር ጸጋ ሰለሞን እንደተናገሩት፤ በዳያስፖራዎች አማካኝነት መሰጠት የተጀመረው "ብሩህ ትውልድ" የኮምፒውተር ፕሮግራሚንግ ስልጠና ለተማሪዎች ክህሎት ማደግ ወሳኝ ድርሻ ይኖረዋል።

ከጥር 8 ጀምሮ ለቀጣይ ሶስት ሳምንታት እየተሰጠ በሚገኘው የኮምፒውተር ፕሮግራሚንግ ስልጠና ያደጉት አገራት በቴክኖሎጂው የደረሱበት ደረጃና ቀጣይ የፈጠራ ክንውኖችን በተመለከተ ማብራሪያ ይሰጣል ሲሉ ተናግረዋል።

የጌት ፋክት ኢትዮጵያን ከመሰረቱ አንዱ የሆኑት መስራችና የናሳ ሳይንቲስቱ ዶክተር ብርሃኑ ቡልቻ በበኩላቸው፣ ስልጠናው የሚሰጠው የማህበረሰቡን ተግዳሮቶች መፍታት በሚረዱ ጉዳዮች ላይ ተማሪዎች እራሳቸውን ብቁ እንዲያደርጉ ለማስቻል ነው።

ዳያስፖራው ማህበረሰብም ለአገሩ ልጆች የሚጠቅሙ ስልጠናዎችን መስጠቱ ሀገርን የማገዝ አንድ አካል ተደርጎ ይወሰዳል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በስልጠናው ዳያስፖራው ያካበተውን የቴክኖሎጂ እውቀትና ክህሎት ወደ ሀገር ቤት ማሸጋገር ብቻ ሳይሆን ወጣቶችን በቴክኖሎጂ እውቀትና ክህሎት ማብቃት፣ ዳያስፖራዎች ሀገራቸውን የሚያግዙበት ሁኔታ በመፍጠር ረገድ መነቃቃት ለመፍጠር ያለመ መሆኑን ጠቁመዋል።

በርካታ ዳያስፖራዎች በውጭ አገራት የተለያዩ ዘርፎች ላይ ተሰማርተው ያካበቱትን ዕውቀትና ክህሎት ወደአገራቸው መጥተው በተመሳሳይ ስልጠና ላይ እንዲያውሉ የሚረዱ መድረኮች በቀጣይ በስፋት ማዘጋጀት ይገባል። ተመሳሳይ ስልጠናዎችን በማብዛት ወጣቶችን በፈጠራና ክህሎት የዳበሩ ማድረግ ይቻላል ብለዋል።

ስልጠናው በኢትዮጵያ ዳያስፖራ አገልግሎትና በጌት ፋክት ኢትዮጵያ አስተባባሪነት እየተሰጠ ይገኛል።

## የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃን ማሰራጨት ስለሚያስከትለው ተጠያቂነት የኅብረተሰቡን ግንዛቤ ማዳበር ይገባል

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡- የጥላቻ ንግግርና ሐሰተኛ መረጃን ማሰራጨት በወንጀል የሚያስቀጣ ቢሆንም የኅብረተሰቡ ግንዛቤ እምብዛም በመሆኑ ማዳበር እንደሚገባ የሕግ ምሁራን ገለፁ፡፡

ጠበቃና የህግ አማካሪ አቶ ፋሲል ስለሺ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የመረጃ ነጻነት አዋጁ ከለውጡ በኋላ በቅርቡ የወጣ እንደመሆኑ ኅብረተሰቡ በአዋጁ ላይ ያለው ግንዛቤ እምብዛም ነው፡፡

ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ህግ እንደመሆኑ ይህን ህግ ለመቀበል የፈረሙ ሀገራት ለማክበርና ለማስከበር ይገደዱበታል፡፡ ኢትዮጵያም ይህን ህግ ለመቀበል ከፈረሙ ሀገራት አንዷ በመሆኗ በኢፌዴሪ ህገመንግስት የተከበረ ነው ፡፡

ሆኖም ግን ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ያልተገደበ አይደለም፡፡ የጥላቻ እና ሐሰተኛ የመረጃ ስርጭትን ለመከላከል በወጣው አዋጅ የጥላቻ ንግግር ማድረግና ሐሰተኛ መረጃን ማሰራጨት በወንጀል የሚያስቀጣ ቢሆንም የኅብረተሰቡ ግንዛቤ አናሳ መሆኑ በተለይ በማኅበራዊ ሚዲያዎች ላይ ችግሮች እንዲሰፉ አድርጓቸዋል፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ያለውን ግንዛቤ ማዳበር ይገባል፡፡

በመሆኑም ማንኛውም ሰው የጥላቻ ንግግርን በአንድ ሰው ወይም በተወሰነ ቡድን ላይ ማንነትን፣ ዘርን፣ ሀይማኖትን፣ ፆታን እና አካል ጉዳተኝነትን መሰረት በማድረግ ሆነ ተብሎ ጥላቻን፣ መድሎን ጥቃትን የሚያነሳሳ ንግግር በብሮድካስት፣ በህትመት፣ በማህበራዊ ሚዲያዎች አማካኝነት በምስል፣ በድምጽ አልያም በስእል ማሰራጨት የተከለከለ ቢሆንም በተለያየ መንገድ እነዚህ ወንጀሎች እየተፈፀሙ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡


አቶ ፋሲል ስለሺ


አቶ ካፒታል ክብሬ

እነዚህን ወንጀሎች የፈፀመ ማንኛውም ግለሰብ በሕጉ መሰረት እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም እስከ ብር 100 ሺህ ብር ያልበለጠ እንደሚያስቀጣ በመጥቀስ፤ በተደረገው የጥላቻ ንግግር በግለሰቡ ወይም ቡድኑ ላይ ጥቃት የተፈጸመ ከሆነ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት በእስራት እንደሚያስቀጣ አብራርተዋል፡፡

ይሁን እንጂ በሀገሪቱ አዋጁ አዲስ በመሆኑ የተነሳ ያለው አተገባበር ያደገ እንዳልሆነ የጠቀሱት አማካሪው፤ ሕግን አለማወቅ ከተጠያቂነት የሚያድን ባለመሆኑ ከመቅጣት ቀደም ብሎ ግንዛቤ መጨበጥ የተሻለ ነው ሲሉ አሳስበዋል፡፡

የህግ ባለሙያ አቶ ካፒታል ክብሬ በበኩላቸው፤ በማህበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ዙሪያ በቂ ግንዛቤ አለመኖሩን ገልፀው፤ የማህበራዊ ትስስር ገፆችን ለማራመድ፣ ስራን ለመፍጠር ማዋል ሲገባ እርስ በእርስ ለመጠፋፋት እየዋለ ይገኛል ብለዋል፡፡

በህገ መንግስቱ ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመረጠውን ሃሳብ የመያዝ፣ የመናገር መብቱ የተጠበቀ እንደሆነ በማብራራትም ሆኖም ፤ ይህ መብት ምንም አይነት ገደብ የማይጣልበት አይደለም ሲሉ አስረድተዋል፡፡

የህግ ባለሙያው እንደገለጹት፤ ይህንን መነሻ አድርጎ በወጣው አዋጅ በአንድ ቡድን፣ ግለሰብ ላይ የጥላቻ ወይም የመረጃው እውነተኛነት በቂ ጥናት ሳይደረግበት የሚሰራጭ ጥቃትን፣ ሁከትን፣ ጥላቻን የሚቀሰቅስ መረጃ ማሰራጨት ከቀላል እስከ ከባድ ቅጣት ያስቀጣል፡፡

የመናገር መብት የማይሸራረፍ መብት ቢሆንም፤ ክብራቸውን፣ ደህንነታቸውን የሚጋፋ ነገር የተፈጸመባቸው አካላት የመጠየቅ መብት እንዳላቸው ገልፀው፤ እንደዚህ አይነት የሕግ ጥሰቶች ሲፈጸሙ የሰዎች ሀብት፣ ደህንነት አደጋ ላይ ስለሚወድቅ የጸጥታ አካላት በህግ ተጠያቂ ማድረግ ይኖርባቸዋል ሲሉ አስረድተዋል፡፡ ህጉ በቅርቡ በመውጣቱ የኅብረተሰቡን ግንዛቤ ማሳደግ ይገባልም ብለዋል፡፡

## በክልሉ አምስት ቢሊዮን ብር የወጣባቸው የገጠር ትራንስፎርሜሽን ማዕከላት ለአገልግሎት ዝግጁ ሆነዋል

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል ከአምስት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ የተደረገባቸውና በተለያዩ አካባቢዎች የተገነቡ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ማዕከላት ለአገልግሎት ዝግጁ መሆናቸውን የኦሮሚያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታወቀ፡፡ ለቡልቡላ አግሮ ኢንዱስትሪ እና የገጠር ትራንስፎርሜሽን ማዕከላት ግንባታ 10 ቢሊዮን ብር ኢንቨስት ተደርጓል፡፡

የኦሮሚያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሰናይት መብሬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ክልሉ የኢንዱስትሪ አብዮትን በማፋጠን ላይ መሆኑንና በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ነው፡፡ በዚህም በአግሮ ኢንዱስትሪው ሰፋ ያለ ለመስራትና የአርሶ አደሮችን ተጠቃሚነትም ለማረጋገጥ ቡልቡላ አግሮ ኢንዱስትሪ ግንባታ ተጠናቆ በአሁኑ ወቅት ባለሀብቶች ወደ ፓርኩ በመግባት ሥራቸውን እያከናወኑ ነው፡፡

በተጨማሪም በተለያዩ ስድስት የክልሉ ስፍራዎች ጥራታቸውን ጠብቀው የተገነቡ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ማዕከላት መኖራቸውንና እነዚህም ባለሀብቶችን እየተጠባበቁ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ የኦሮሚያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽንም ሆነ ሌሎች ተቋማትም ባለሀብቶች በፍጥነት ፈቃድ አግኝተው ወደ ሥራ እንዲገቡና የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት እንዲወጡ አስፈላጊው ድጋፍና ትብብር እንደሚደረግላቸውም ዋና ሥራ አስፈፃሚዋ አረጋግጠዋል፡፡ በመሆኑም ባለሀብቶችም ወደእነዚህ አካባቢዎች በመሄድ እንዲያለሙ አሳስበዋል፡፡


ዋና ሥራ አስፈፃሚ ሰናይት መብሬ

የኮርፖሬሽኑ ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ተስፋዬ ጀማማ በበኩላቸው፤ የቡልቡላ አግሮ ኢንዱስትሪ በ271 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ለባለሀብቶች ለማስተላለፍ 135 ሄክታር መሬት መልማቱን ጠቁመዋል፡፡ የተቀረው ደግሞ በተወሰነ ደረጃ መሠረተ ልማቶች ያረፉበት በመሆኑ ባለሀብቶችን ለመሳብና ለማስተናገድ ምቹ ሁኔታ መኖሩን ገልፀዋል፡፡ በቂ መሠረተ ልማት የተሟላላቸውና ደረጃቸውን የጠበቁ ለ248 ባለሀብቶች የሚሆኑ መኖሪያ ቤቶችን የያዘ ስለመሆኑም አብራርተዋል፡፡

እንደ አቶ ተስፋዬ ገለፃ፤ ከቡልቡላ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ በተጨማሪ ስምንት የገጠር ትራንስፎርሜሽን ማዕከላት ታሳቢ ተደርገው እንደነበርና በአሁኑ ወቅት ሻሸመኔ፣ አርሲ፣ ዶዶላ፣ ወለንጪቲ፣ አዳማ እና ባቱ ላይ መገንባታቸውንና እያንዳንዳቸው በ10 ሄክታር መሬት ላይ ያረፉ መሆናቸውን አብራርተዋል፡፡ እነዚህ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ማዕከላት የአስተዳደር፣ ከፊል ፕሮሰስ የሚያደርግበት ስፍራ፣ የገበያ ማዕከል፣ መጋዘንና ሌሎች ሼዶችንም በውስጡ ያቀፈ መሆኑንም አስረድተዋል። ባለሀብቶችም በእነዚህ ማዕከላት ገብተው ማምረት እንደሚችሉ ጠቁመዋል፡፡

የአግሮ ኢንዱስትሪ ፓርኩም ሆነ የገጠር ትራንስፎርሜሽን ማዕከላት ዋነኛ ዓላማ አርሶ አደሮችና የክልሉን ነዋሪዎች አኗኗር በማዘመን የበለጸገች ኢትዮጵያን መፍጠር ነው፡፡ ለዚህም ሲባል መንግስት ለቡልቡላ አግሮ ኢንዱስትሪና የገጠር ትራንስፎርሜሽን ማዕከላት ግንባታ 10 ቢሊዮን ብር ኢንቨስት ማድረጉንም ምክትል ዋና ሥራ አስፈፃሚው አረጋግጠዋል፡፡

ዜና



አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ



አምባሳደር ደሴ ዳልኬ



አምባሳደር ደሚቱ ሐምቢሳ



አምባሳደር ኢንጂነር መላኩ እዘዘው

# አምባሳደሮች ለኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ልዩ ትኩረት መስጠታቸውን ገለጹ

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

አዲስ አበባ፡- አምባሳደሮች የኢትዮጵያን ጥቅም በሚያስከብሩና ለሀገሪቱ ዕድገት በሚበጁ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥተው እየሠሩ መሆናቸውን በተለያዩ ሀገራት ኢትዮጵያን ወክለው የሚሰሩ አምባሳደሮች አስታወቁ፡፡

የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች እና የግሉ ዘርፍ የውይይት መድረክ በሂልተን ሆቴል ከትናንት በስቲያ በተካሄደበት ወቅት በጣሊያን የኢትዮጵያ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ደሚቱ ሐምቢሳ እንደተናገሩት፤ የኢትዮጵያንና የጣሊያን የቆየ ሁለትዮሽ ወዳጅነት ለማጠናከርና የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም በሚመጥኑ ሥራዎች ላይ ልዩ ትኩረት መስጠታቸውን ገልፀዋል፡፡ በዚህም በርካታ ውጤቶች መመዝገባቸውን ጠቁመዋል፡፡

እንደ አምባሳደሯ ገለፃ፤ በጣሊያን በሚገኘው የኢትዮጵያ ኤምባሲ አምባሳደር እና ሌሎች ባለሙያዎች ያላሰለሰ ጥረት በማድረግ የጣሊያን ካምፓኒዎች በኢትዮጵያ ኢንቨስት እንዲያደርጉ በትኩረት መሥራቱን ጠቁመዋል፡፡ በዚህም በቢሊዮን ዶላር አቅም ያላቸው ባለሀብቶችና ድርጅቶች በኢትዮጵያ በተለያዩ አካባቢዎች መዋዕለንዋያቸውን ስራ ላይ ማዋላቸውንና ሀገርና ዜጋ ተጠቃሚ መሆናቸውን አስረድተዋል፡፡ በቀጣይም የኢትዮጵያን ጥቅም በሚያስጠብቁና በሁለቱ ሀገራት መካከል ያሉ የግል ዘርፍ በተናበበ ሁኔታ እንዲሰሩ በልዩ ሁኔታ አጽንኦት ሰጥተው እንደሚሠሩ አረጋግጠዋል፡፡

በደቡብ ኮሪያ የኢትዮጵያ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ደሴ ዳልኬ በበኩላቸው፤ በአምባሳደርነት ሥራቸው በዋናነት የኢትዮጵያን ጥቅም በሚያስከብሩና የሁለቱን ሀገራት ወዳጅት በሚያጠናክሩ ተግባራት ላይ ትኩረት መስጠታቸውን አስገንዝበዋል፡፡ በተለይም ደግሞ በደቡብ ኮሪያ አቅም ያላቸው የቴክኖሎጂ ኩባንያዎችና ግዙፍ ድርጅቶች መዳረሻቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲያደርጉ ከፍተኛ የማግባባት ሥራ እየሰሩ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ተስፋ ሰጪ ተግባራትም መኖራቸውን አስገንዝበዋል፡፡ በቀጣይም የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስጠበቅ በሁለቱ ሀገራት እና የግሉ ዘርፍ መካከል የጠነከረ ወዳጅነት እንዲኖር አበክረው እንደሚሰሩ ገልፀዋል፡፡ በተለይም ደግሞ ለኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ልዩ ትኩረት እንሰጣለን ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ኢንጂነር መላኩ እዘዘው በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች እና የግሉ ዘርፍ የውይይት መድረክ ዘርፍ ብዙ ዓላማዎችን ያነገበ መሆኑን ጠቁመው፤ ከነባር እና አዳዲስ ዲፕሎማቶች ጋር መተዋወቅ፣ በንግድ ምክር ቤቱ እና በዲፕሎማቶች መካከል መልካም የሥራ ግንኙነት በማድረግ የሀገሪቱ ንግድና ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ በጋራ መስራት፣ የውጭ ባለሀብቶችን ወደ ኢትዮጵያ በመሳብ የኢንቨስትመንት ዕድሎች ላይ መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ ለማድረግ፣ በኢትዮጵያ የሚገኙ ባለሀብቶች ወደ ውጭ አገራት በመሄድ ከአቻዎቻቸው ጋር የልምድ ልውውጥ እና የቴክኖሎጂ ሽግግር እንዲያገኙ ለማገዝ የሚያስችሉ ስራዎችን በጋራ ለማከናወን ያለመ ነው፡፡

በተጨማሪም በውጭ አገራት የሚመነጩ የንግድ እና የቴክኖሎጂ መረጃዎች በማግኘት በተግባር ላይ እንዲውል ለማድረግ፣ በተለያዩ አገራት በሚዘጋጁ የንግድ ትርዒቶች ተሳትፎ ላይ በመገኘት በጋራ መስራት የሚቻልባቸው ሁኔታዎችን ለማመቻቸት፣ የኢትዮጵያ ወጪ ምርቶች በውጭ አገራት ተቀባይነት እንዲያገኙ በጋራ ለማስተዋወቅ፣ ከሀገራቱ ዲፕሎማቶች ጋር የሰመረ ግንኙነትን ለማጎልበት በማሰብ መሆኑን ጠቁመው አምባሳደሮች እነዚህን ተግባራት እውን ለማድረግ ከፍተኛ ሚና መወጣት ስለሚችሉና ዕድሉም ስላላቸው ትኩረት እንዲሰጡትና ከንግድ ምክር ቤቱ ጋር የጠነከረ ወዳጅነት እንዲፈጥሩም ጠይቀዋል፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ እንደተናገሩት፤ አምባሳደሮች ከመንግስትና ከግል ዘርፍ ጋር በተናበበ ሁኔታ መስራት ይጠበቅባቸዋል። በውጭ ሀገር በሚካሄዱ ባዛሮች፣ ኤክስፖዎችና ሌሎች ሁነትን በማነፍነፍ የኢትዮጵያን ገጽታ የሚገነቡና ብሄራዊ ጥቅምን የሚያስከብሩ ስራዎች ላይ ማተኮር ይገባል።

በአሁኑ ወቅት የሀገሪቱ ሁኔታ እጅግ ተስፋ ሰጪ ሲሆን፤ የኮርና ቫይረስ ስርጭት በተገታበት ወቅት በመሆኑ የተሻለ ሥራ ለመከወንም ጥሩ አጋጣሚ መሆኑን አስገንዝበዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለፃ፤ አምባሳደሮች የሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች በተጠና መንገድ መከናወን አለባቸው። በተለይም ኢትዮጵያ ያላትን ጸጋ ለማስተዋወቅ በየትኛው ሀገር ምን መሥራት አለበት የሚለውም ልዩ ትኩረት ይፈልጋል ብለዋል። በአሁኑ ወቅት በጥሩ ሁኔታ እየተነሳ ያለውን ገጽታ የበለጠ ለማሻሻል በትኩረት መስራት እንደሚገባም አሳስበዋል።

## በጦርነቱ የተጎዳው...

አስፈላጊ ነው ። ያለ ሰላም ግብርና ፣ ኢንዱስትሪ ፣ ንግድ ማካሄድ አይቻልም ፣ ግብርና ግብዓቶች አርሶ አደሩ ጋር ለማድረስ ፣ አርሶ አደሩ ለማምረት ፣ ያመረተውን ምርት ለመሰብሰብ ቅድሚያ ሰላም ሊኖር እንደሚገባ ይገባል።

ሰላም በሌለበት ኢኮኖሚ አይኖርም ፣ ቢኖርም ስኬታማ ሊሆን አይችልም። ሶማሊያ ፣ሊቢያ፣ሶሪያ፣ ኮንጎ ዲሞክራትክ ሪፐብሊክ ለዚህ ምሳሌ ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ሀገራት ለገቢ ምንጭ የሚሆን የተጠራቀመ የማዕድን ሀብት እያላቸው በሰላም እና ፀጥታ ምክንያት የኢኮኖሚ መስመሮች በመውደማቸው ኢኮኖሚያቸው ችግር ውስጥ ወድቋል።

በኢትዮጵያ ከሰላም ስምምነቱ በኋላ የጦርነት ሰለባ የሆኑ አካባቢዎችን መልሶ ለማቋቋም ብዙ ወጪ እንደሚጠይቅ አያጠያይቅም ያሉት ዶክተር ጉቱ፤ ለመልሶ ግንባታና ለጥገና ትኩረት በመስጠት ነገሮች ወደቀደመው ሁኔታ እንዲመለሱ ማድረግ ለኢኮኖሚው መነቃቃት ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል ብለዋል።

በጦርነቱ የኢኮኖሚ መስመሮች የመቋረጥ እድል ገጥሟቸዋል ። የሻኪሶ ማዕድን ምርት ስራ ላይ አይደለም፣ በትግራይና በአፋራባች ክልሎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በጦርነቱ ምክንያት ተቋርጦ ቆይቷል። ሰፊ የቱሪዝም እንቅስቃሴ የሚካሄድበት የሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍሎች በመሰል ችግሮች ትራንስፖርት ቆሟል ብለዋል።

እንደ ዶክተር ጉቱ ገለጻ ፤ የሰላም እጥረት ለኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ከብድር እና ከቴክኖሎጂ በላይ አደጋ አለው። ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። የሰላም እጥረት የሰው ኃይል ካለበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተንቀሳቅሶ ለኢኮኖሚ ልማት እንዳይውል ያደርጋል። ካፒታል ከአንድ ማዕዘን ተነስቶ ወደሌላ ማዕዘን እንዳይንቀሳቀስ ያደርጋል ፣ የተመረቱ ምርቶች ወደ ዉጪ ሀገር ተልከው የውጪ ምንዛሪ ገቢ የማስገኘት አቅም እንዳይኖራቸው ያደርጋል ብለዋል።

" ኢኮኖሚ ሰላም ነው ፣ ሰላም ኢኮኖሚ ነው" ያሉት ዶክተር ጉቱ፤ ሰላም ኢኮኖሚውን ውጤታማ የሚያደርገው በተበጣጠሰ መልኩ ሳይሆን ሁሉንም በአማከለ መልኩ ተደራሽ ሲሆን ነው ። በአንድ ሀገር ውስጥ የኢኮኖሚና ሰላም አንድ ሳንቲም ገጽታነት የሚገለጸው በሁሉም ማዕዘናት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን በማይበጣጥስ መልኩ እኩል ተደራሽ ማድረግ ሲቻል ነው ሲሉም ተናግረዋል።

ሰላም ከሰፈነ በኋላ የኢኮኖሚ መሰረተ ልማቶች ፣ የኢኮኖሚ ተቋማት ፣የኢኮኖሚ ስርዓቶች መልሶ መገንባት እና ጥገና ላይ ትኩረት መደረግ አለበት። በተለይ ጦርነት ሲደረግባቸው በነበሩ አካባቢዎች በተለያዩ ኢንቨስትመንት ዘርፎች ባለሀብቶች በራሳቸው በመተማመን በፍጥነት በኢኮኖሚው ውስጥ እንዲሳተፉ ለማድረግ ጉልህ ሚና ይኖረዋል ብለዋል።

## "ኢትዮጵያ ለአየር ንብረት ...

የኢኮኖሚ ዕቅድ ቀርጻ ተግባራዊ እያደረገች እንደምትገኝም አብራርተዋል።

አዲሱ እቅድ በግሉ ዘርፍ የሚመራ፣ተወዳዳሪ፣ ሀብት ቆጣቢ እና ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የኢንዱስትሪ ኢኮኖሚ ሽግግርን በማሳለጥ ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገትን ለማስፈን ያለመ መሆኑንም ነው በጉባኤው ላይ የገለጹት።

አገር በቀሉ የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብሩ በዘላቂ ዕድገት መርሆዎች የተደገፈ በመሆኑ፤ ለግብርና፣ ለማኑፋክቸሪንግ፣ ለቱሪዝም፣ ለኢኮኖሚ ዕድገት ቁልፍ ምሰሶዎች ቅድሚያ እንደሚሰጥም ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ሁሉን አቀፍ የብልጽግና አጀንዳዎች ለዜጎች መተዳደሪያን የፈጠረ እና ለትውልድም የሚተርፍ አረንጓዴ ኢኮኖሚን መሰረት ያደረገ ተግባር ማከናወኑን ጠቁመዋል።

በአሁኑ ወቅት ግን ለአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭ ከሆኑ በርካታ ታዳጊ ሀገራት አንዷ ኢትዮጵያ ነች ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶክተር)፤ የተጋላጭነት ሁኔታውን ግምት ውስጥ በማስገባት በኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም ዘርፎች የአየር ንብረት ለውጥ መላመድ ተካትቶ እየተሰራ ነው ብለዋል።

ተጽእኖውን ለመቋቋም ኢትዮጵያ የድርሻዋን በመወጣት በቁርጠኝነት እየሰራች እና የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ የሚያስችሉ በርካታ ተግባራት እያከናወነች ትገኛለች ሲሉም ነው የገለጹት።

ኢትዮጵያ የታዳሽ ኃይሎች ባለቤት መሆኗን በመጠቀምም፤ ከውሃ፣ ከነፋስ፣ ከጸሃይ እና ከእንፋሎት ሃይል በማመንጨት ላይ እንደምትገኝም ተናግረዋል። እነዚህን እምቅ ሀብቶች መሰረት በማድረግ እአአ 2050 የካርበን ልቀትን ዜሮ ለማድረስ ትኩረት መስጠቷንም አንስተዋል።

ኢትዮጵያ በጀመረችው የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በተከታታይ አራት አመታት 25 ቢሊዮን ችግኞችን መትከል ችላለች ሲሉም ተናግረዋል። ትግበራው 64 ሚሊየን በጋዝ የሚሰሩ ተሽከርካሪዎች ለአንድ አመት ወደ ከባቢ አየር የሚለቁትን የተበከለ አየር እንደማስቀረት እንደሚቆጠርም አብራርተዋል።

በኢትዮጵያ እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መካከል የንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነትን ለማጠናከር ያለመ የስትራቴጂክ አጋርነት እንዳላቸው በማስታወስም፤ በአገራቱ መካከል ያለው ዘርፈ ብዙ ግንኙነት ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አመልክተዋል።

የኢትዮጵያ የስትራቴጂክ ኢንቨስትመንት ቡድን በሀገሪቱ በተለይ በታዳሽ ሃይል፣ሪል እስቴት እንዲሁም በግብርና ዘርፎች ያሉትን ምቹ የኢንቨስትመንት እድሎችን እንዲጠቀሙ ከተለያዩ የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች ባለሀብቶች ጋር በቅርበት እየተሰራ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በሀገራቱ መካከል ያለው የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ያደረገ ግንኙነት በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት እና ባደጉ ሀገራት መካከል ላሉ ግንኙነቶች እንደምሳሌ ተጠቃሽ እንደሚሆንም ተናግረዋል።

መዋዕለንዋያቸውን ለማፍሰስ ለሚፈልጉ አልሚዎች እና ባለሀብቶች ኢትዮጵያ ያልተነኩ ሀብቶች እና የተፈጥሮ ጸጋዎች ባለቤት መሆኗንም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶክተር) ተናግረዋል። የተባበሩት አረብ ኤምሬቶች አለም አቀፍ ተቋማትን በመገንባት ያስመዘገበችው ስኬት ለኢትዮጵያ መነሳሳትን የሚፈጥር መሆኑንም ነው የገለጹት።

በኢትዮጵያ እና በተባበሩት አረብ ኤምሬቶች መካከል ያለው በመተማመንና በመከባበር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት በርካታ ፍሬዎችን እያፈራ ወደ ላቀ ደረጃ እንደሚያድግ ጥርጥር የለኝም ብለዋል።

የአቡዳቢ የሳስቴኔቢሊቲ(የዘላቂነት) ሳምንት (ADSW) ዘላቂ ልማትን ለማፋጠን እና ኢኮኖሚያዊ፣ማኅበራዊ እና አካባቢያዊ ዕድገትን ለማሳደግ በተባበሩት ዓረብ ኤምሬቶች እና በንጹህ የኃይል ማመንጫ ኩባንያ የተደገፈ ዓለም አቀፍ መርሐ ግብር ነው፡፡

## ተገቢውን የባንክ አገልግሎት...

በባንኩ የተፈጠረውን ችግር ሲጠይቁ ምላሽ የሚሰጣቸው አካል እንደሌለ ጠቅሰው፤ አንዳንዴም ከብሔራዊ ባንክ በተላለፈ መመሪያ መዘጋቱን በኢመደበኛ መንገድ እንደሚሰሙ ተናግረዋል።

ዱብቲ ከተማ ያለ የባንክ ቅርንጫፍ ላይ ገንዘብ በጥሬው ወስደን ወደሂሳባችን ማስገባት የምንችል ቢሆንም ከዱብቲ ከተማ ውጪ ባሉ ሌሎች ባንኮች ላይ የሂሳብ እንቅስቃሴ እንዳይኖረን ተደርጓል የሚሉት አቶ መሀመድ፤ ከሌሎች ባንኮችም ወደ ዱብቲ ቅርንጫፍ ማስገባት እንደማይቻል አክለው ጠቅሰዋል።

ከዱብቲ ባንክ ቅርንጫፍ ያወጡትን የሂሳብ ደብተር ይዘው ሌላ ቦታ አገልግሎት ለማግኘት እንደሚቸገሩ እና ሂሳባችሁ ዝግ ነው እንደሚባሉ በመግልጽም በአሁኑ ወቅት ተሻሽሎ እንጂ በሚያወጡት የገንዘብ መጠን ላይም ገደብ ተጥሎ እንደነበር አንስተዋል።

ሌላው የዱብቲ ከተማ የንግድ ባንክ ደንበኛ አቶ ይርጋለም ሰኢድ በበኩላቸው፤ የተለያዩ ችግሮች በባንኩ አገልግሎት ላይ እንዳሉ ገልጸው፤ 16 ኪሎ ሜትርና ከዚያ በላይ ርቀት ተጉዞ ሌላ የባንክ አካውንት በመክፈት እየተመላለሱ ለመጠቀም መገደዳቸውን ተናግረዋል።

በባንኩ ለመንግሥት ሠራተኛው ሙሉ አገልግሎት የሚሰጥ ሲሆን፤ ሌላው ማኅበረሰብ ግን አገልግሎት እያገኘ አይደለም ሲሉ ገልጸዋል።

የዱብቲ ከተማዋ ነዋሪ የሆኑት አቶ አህመድ መሀመድም ከላይ የተነሱትን ሃሳቦች እንደሚጋሩ ገልጸው፤በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከዱብቲ ቅርንጫፍ ገንዘባቸውን እንደልብ ማንቀሳቀስ የማይችሉበት ሁኔታ መፈጠሩን ገልጸዋል።

በአካባቢው በሚገኙት ሰመራ አለያም ሎግያ ሄደው ገንዘብ ለማውጣት ሂሳባችሁ ታግዷል የሚል ምላሽ እንደሚሰጣቸው አስረድተዋል።

በአማራ ብሄራዊ ክልል ምዕራብ ጎንደር ዞን የመተማ ወረዳ ገንደውሃ ከተማ ነዋሪ የሆነው ወጣት ዳዊት መልካሙም በከተማቸው በተለይ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች ተመሳሳይ ችግሮች እንዳሉ የገለጸ ሲሆን፤ ኅብረተሰቡ በባንክ አገልግሎት ምክንያት መጉላላት እየደረሰበት መሆኑን ጠቁሟል።

ወጣቱ ችግሩ ከጥቂት ወራት በፊት ጀምሮ እንደተከሰተ እና ቅሬታቸውን ቢያቀርቡም መፍትሄ ሊያገኙ አለመቻላቸውን ተናግሯል። በወረዳው ውስጥ ባሉ የንግድ ባንክ ቅርንጫፎች ሰዎች እንደልብ የተላከላቸውን ገንዘብ መቀበል እንደማይችሉ እና በሂሳብ ደብተሮቻቸው ከሌላ ቅርንጫፍ ገንዘብ ማውጣት እንደማይችሉ በመጥቀስ ጉዳዩ ሕዝብን እያጉላላ መሆኑን በቅሬታ አብራርቷል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጥያቄ ያቀረበላቸው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሰመራ ዲስትሪክት ዳይሬክተር አቶ ሰሚር አማረ፤ በዱብቲ ከተማ የባንክ ቅርንጫፎች ላይ የሚከሰት የአገልግሎት መጓደል ቢኖር በማንኛውም ሰዓት ማስተካከል እንችላለን ያሉ ሲሆን ፤ ሆኖም ደንበኞች ያነሱት ቅሬታ የተፈጠረው በቅርንጫፉ የአገልግሎት መጓደል ሳይሆን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በፃፈው ደብዳቤ አማካኝነት ነው ብለዋል።

ቶጎ ጫሌ፣ ሞያሌ፣ ዶሎ አዶ፣ ዱብቲ እና መተማ ላይ ያሉ ቅርንጫፎች በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመታገዳቸው (ዳውንግሬድ) መደረጋቸውን በመግለጽም፤ የተጠቀሱት አካባቢዎች የመንግሥትም ሆነ የግል ባንኮች ዳውንግሬድ እንዲሆኑ የተደረገው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እአአ ጁን 6/ 2022 በፃፈው ደብዳቤ መሆኑን አብራርተዋል።

በመሆኑም ብሔራዊ ባንክ በፃፈው ደብዳቤ መሰረት ከቅርንጫፎቹ ወደ ሌላ የባንክ ቅርንጫፍ መላክ፣ በባንክ ደብተሮቹ ከሌላ ቅርንጫፍ ማውጣት እና እንደልብ ሂሳብን ማንቀሳቀስ ላይ ችግር መፍጠሩን ጠቁመዋል። ሆኖም የሚሰጡ አገልግሎቶች ከብሔራዊ ባንክ በሚላኩ የማሻሻያ ደብዳቤዎች መሰረት ከጊዜ ወደጊዜ መሻሻል እያሳዩ ነው ብለዋል። በአጠቃላይም በብሔራዊ ባንክ ትዕዛዝ መሰረት እንጂ በባንኩ ቅርንጫፎች በኩል ደንበኞችን ለማጉላላት ተብሎ የተሠራ ሥራ የለም ሲሉ አክለዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጉዳዩን አስመልክቶ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ምላሽ ለማግኘት በስልክም ሆነ በደብዳቤ በመጠየቅ ያደረገው ተደጋጋሚ ሙከራ አልተሳካም።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የጥምቀት በዓል በሰላም እንዲከበር ሁሉም ኃላፊነቱን ይወጣ!

ኢትዮጵያውያን በአንድነት በዓደባባይ ከሚያከብሯቸው፤ ከፍ ያሉ ማኅበራዊ እና መንፈሳዊ እሴቶች ካሏቸው አመታዊ በዓላት መካከል የጥምቀት በዓል አንዱ ነው። በዓሉ ከሃይማኖታዊ ይዘቱ ባሻገር የአከባበር ሥርዓቱ የሚፈጥረው ድምቀት ደግሞ የሀገር ገጽታን በመገንባት ሂደት የላቀ አስተዋጽኦ እያበረከተ ያለ፤ ከሀገር አልፎም በዩኔስኮ በማይዳሰስ ቅርስነት ተመዝግቦም የዓለም ሀብት እስከመሆን የደረሰም ነው።

በክርስትና እምነት አስተምህሮ ቀኑ የዓለም መድህኒት የሆነው እየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ በመጥምቁ ዮሀንስ የተጠመቀበትን ዕለት ለማስታወስ የሚከናወን ቢሆንም፤ ከዚህ ያለፉ ባህላዊ እሴቶችንም ደርቦ የያዘ ነው። ምክንያቱም በዓሉ ከመንፈሳዊ በዓልነቱ በተጨማሪ፣ ባህላዊ እሴቶችን ባካተተ መንገድ በድምቀት መከበሩ፤ ከሃይማኖቱ ተከታዮች ባለፈ ከእምነቱ ተከታዮች ውጪ ያሉ ሰዎችም ቀኑን በጉጉት እንዲጠብቁ አድርጓል። ይሄ ደግሞ ለበዓሉ ተጨማሪ ድምቀትና ውበት ሆኗል።

"ለጥምቀት ያልሆነ..." እንዲሉ፤ የእምነቱ ተከታዮች በዕለቱ ተውበውና አምረው አደባባዮችን ማድመቃቸው፤ ካህናቱ ልብሰ ክህነታቸውን ለብሰው፣ መዘምራኑ የተለያዩ ጌጠኛ ልብሶቻቸውን ለብሰው በመንፈሳዊ ኅብረ ዜማ ለበዓሉ ድምቀት ሆነው በየአደባባዩ ተውበው መታየታቸው ውበቱን የሚያጎላና ከመንፈሳዊነቱ ባሻገርም በብዙዎች እንዲጠበቅም የሚያደርጉ ናቸው፡፡

በዓሉ በአለም አቀፍ ደረጃ በዩኔስኮ እውቅና ካገኙ ዓለም አቀፍ የአደባባይ በዓላት አንዱ የመሆኑ እውነታም በራሱ፣ በዓሉ ከሀገር ውስጥ ባለፈ ዓለም አቀፍ እውቅና እንዲያገኝ አስችሎታል። በዚህም በሀገር ገጽታ ግንባታ ላይ ሊኖረው የሚችለውን አስተዋጽኦ ከፍ አድርጎታል። ይሄ ደግሞ የበዓሉን መንፈሳዊና ባህላዊ እሴቶችን ከማጎልበት ባለፈ፤ የቱሪዝም ኢንዱስትሪው ላይ እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ከፍ እንዲል አድርጎታል። በቀጣይም ሊኖረው የሚችለው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።

በዓሉ ከፈጠረው ዓለም አቀፍ ትኩረትም ጋር በተያያዘ በበዓሉ ላይ ለመታደምና ለማክበርም ጭምር ከተለያዩ የዓለም ሀገራት የሚመጡ ቱሪስቶች ቁጥር እየጨመረ ነው፤ ይህም ሀገሪቱ ድህነትን አሸንፋ ለመውጣት ለጀመረችው ትግል ትልቅ አቅም እንደሚሆን ይታመናል፡፡

በዚህ መልኩ የሚገለጸው የጥምቀት በዓል ታዲያ ከመንፈሳዊ ክዋኔው ባለፈ ባህላዊ እሴቶችን ባከበረ እና የቱሪዝም ሀብትነቱ በሚጎለብትበት መልኩ በሰላም አክብሮ መዋል ትልቅ ቦታ ሊሰጠው የሚገባ ነው፡፡ በዓሉን በሰላም ማክበር እንደ ሀገር ያለውን መንፈሳዊ ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን አስጠብቆ ለማስቀጠል ወሳኝ ነው ።ለዚህ ደግሞ የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት ከፍ ያለ ነው።

በተለይም የእምነቱ ተከታዮች የበዓሉን ሁለንተናዊ ጠቀሜታ በአግባቡ በመረዳት በሰላም ተጀምሮ በሰላም እንዲጠናቀቅ የበኩላቸውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ለዚህ የሚሆን መንፈሳዊ እና አእምሯዊ ዝግጁነትም ይጠበቅባቸዋል። መላው ሕዝብም የበዓሉን መንፈሳዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ በአግባቡ በመረዳት በዓሉ በሰላም ተከናውኖ እንዲያልቅ የተቻለውን ሁሉ ማበርከት ይኖርበታል። ለበዓሉ በስኬት መጠናቀቅ ዘብ መቆም ይጠበቅበታል።

የጸጥታ ኃይሎችም በዓሉ በሰላም እንዲከበር ከሕዝቡ ጋር በተሻለ ቅንጅት መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል፤ በተለይም በዓሉ የአደባባይ በዓል ከመሆኑ አንጻር ሊኖራቸው የሚገባው ዝግጁነት ከፍ ያለና አስተማማኝ ሊሆን ይገባል። በዓሉን የእኩይ ዓላማቸው ማስፈጸሚያ ለማድረግ ከሚፈልጉ የውስጥ ሆነ የውጪ ኃይሎች ለመታደግ የጥፋት ኃይሎችን እንቅስቃሴ በትኩረት መከታተል እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፈጣን እርምጃ መውሰድ የሚያስችል ዝግጁነት መፍጠር ያስፈልጋል። ከሰሞኑ በጸጥታ ኃይሎች እየተወሰዱ ያሉ ሰላም የማስከበር ሥራዎችም ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል።

በተለይም አሁን እንደ ሀገር ካለንበት የጦርነት ማግስት ሀገራዊ እውነታ አንጻር፣ በዓሉ በሀገሪቱ እየመጣ ያለውን ሰላም በተጨባጭ ለመላው ዓለም ለማሳየት መልካም አጋጣሚ ስለሚሆን፤ ይህንን አጋጣሚ በአግባብ ልንጠቀምበት ያስፈልጋል። በዓሉን ለመታደም ከተለያዩ የዓለም ሀገራት የመጡ ቱሪስቶች የሀገር ውስጥ ቆይታቸው ሰላማዊና አስደሳች እንዲሆንና ተመልሰው እንዲመጡ የተሻለ ዕድል ለመፍጠር በኢትዮጵያዊ እንግዳ ተቀባይነት መንፈስ ማስተናገድ ይገባል!

ከዚህ ጎን ለጎንም እየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት ፣ የተጠመቀበት በኋላም የሞተበት ትልቁ አላማ እርቅ መሆኑን በማሰብ አሁን ያለንበትን የእርቅ መንገድ ወደ ላቀ ስኬት የሚሄድበትን መንገድ አይናችንን ከፍተን ማየት ይጠበቅብናል።


አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

# "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" የሙሰኞች ብሂል

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

የኢትዮጵያ ሕዝብ ጥበበኛ ሕዝብ ነው፤ ጥበቡ ይገርመኛል። ማስተዋል እና ምሳሌው ያስደንቀኛል። ነገሮችን፣ አጋጣሚዎችን፣ ሁኔታዎችን በምሳሌያዊ ንግግር ሲገልጽ ሳይንስን የሚያስንቅ ጥበብ አለው። ከዚህ ምሳሌያዊ ንግግሩ መካከል ለሙሰኛ ባለሥልጣን የሚመጥን አንድ አባባል መዘዝኩ፤ "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይበቀል የሚል" አህያዊ አባባል። ይሄ አባባል አህያን ከግብሯ ለማሳነስ የተነገረ አይደለም፤ ይልቁንም በአባባል ሂደቷ ላይ ተመሥርቶ የሚታይባትን ባሕሪ ያገናዘበ ገለጻ እንጂ፤ እኔም ይሄን የራስ ወዳዶች ስሜት ለሙሰኛ ባለሥልጣናትና ላልተገባ ተግባራቸው ስጠቀምበት ሀሳቤን በትክክል ይገልጽልኛል ብዬ በማሰብ ነው፡፡

ሙሰኞችን በአንድ ቃል ግለጽልኝ ብትሉኝ ከአህያ ጋር አዛምዳቸዋለሁ። አህያ ሰርዶ ስትግጥ ለነገ የሚል እሳቤ የላትም። ምክንያቱም ለነገ ማቆጥቆጥ እንዳይችል ጭምር አድርጋ ሥሩን ነቅላ ትበላለችና ነው። በዚህም ለሚመጣው ትውልድ ርህራሄን አጥታ ሰርዶ እንዳይበቅል፣ ግጦሽ እንዳይለማ የምታስብና አሁናዊ ራሷን ብቻ የምትሻ እንስሳ ሆና በአባባሉ ላይ ቀርባለች። አህያ ራስ ወዳድና ለእኔ ብቻ የምትል ሆና ተስላ በሥነ ቃሉ ላይ ቀርባለች። በአህያ ልብ ውስጥ ለነገ የሚል ማስተዋል የለም፤ በአህያ ልብ ውስጥ ርህራሄ የለም። ለሌሎች ማሰብና፣ ለሌሎች መኖር የለም። ተጀምሮ እስኪያልቅ ድረስ የራሷ ብቻ ናት። ይሄን እውነት ወደ ሙሰኛ ባለሥልጣናትና ወደ ግብራበሮቻቸው ስናመጣው ከአህያ ግብር ጋር አንድ ሆኖ እናገኘዋለን።

ሙሰኞች ለመጪው ትውልድ የሚያስብ ከእኔነት የተረፈ አስተሳሰብ የላቸውም። ልክ እንደ አህያና እንደ አስተሳሰቧ ስለሚግጡት ሳር፣ ስለሚያግበሰብሱት ሃብት ብቻ ነው የሚያስቡት። በማንነታቸው ውስጥ ሰውኛ ባሕሪ የለም። ለሚመጣው ትውልድም ሆነ ላለው ትውልድ የሚሆን ቅንጣት ርህራሄ ያልፈጠረባቸው ከእኔነትና ከብቻ እሳቤ ያልተላቀቀ እንስሳዊ ተፈጥሮ ያላቸው ናቸው። ማን ወደ ሥልጣን እንዳመጣቸው፣ ለምን እንደመጡ፣ መጥተውስ ምን እንደሚሠሩ ያውቃሉ ቢባል እንኳን፤ እነሱ ግን በዛ እውነት ውስጥ አይደሉም። ሙሰኞች ወደ ሥልጣን ያመጣቸውን ድሀ ሕዝብ በመጠቀም ራሳቸውን በመጥቀም ሥራ ላይ የተጠመዱ ናቸው። ማኅበረሰብ ለማገልገል የሚሆን የሞራል ልዕልና የላቸውም። ለዚም

**ሙሰኞች ወደ ሥልጣን ያመጣቸውን ድሀ ሕዝብ በመጠቀም ራሳቸውን በመጥቀም ሥራ ላይ የተጠመዱ ናቸው። ማኅበረሰብ ለማገልገል የሚሆን የሞራል ልዕልና የላቸውም**

ነው በመስረቅና በመዋሸት፣ በመስጠትና በመቀበል ሕገ ወጥ ድርጊት ውስጥ የሚሳተፉት፡፡

ሙሰኞች ከኢትዮጵያ አብራክ የበቀሉ ናቸው። ኢትዮጵያ ሀገራችን ይጠሩኛል ብላ በችግር ያሳደገቻቸው፣ አስተምራ ለቁም ነገር ያበቃቻቸው ናቸው። ከየትም አልመጡም፤ የበቀሉት ከማኅበረሰቡ ውስጥ ነው። እያሰቃዩ ያሉትም ማኅበረሰቡን ነው። እኩይ ድርጊታቸውን የተለማመዱበት መንገድ ይለያይ እንጂ ማኅበረሰቡ ወልዶ ያሳደጋቸው ናቸው። የሚገቱትም በማኅበረሰቡ ነው። በመሆኑም ማኅበረሰቡ እነዚህን የአገልጋይነት ዓላማ የሌላቸውን ሙሰኞች እያጋለጠ እንስሳዊ ድርጊታቸውን መግታት አለበት። ከድሀ እናት መቀነት በተከፈለ ገንዘብ ተምረውና ለቁም ነገር በቅተው በድህነት ያስተማረቻቸውን ሀገራቸውን መዝረፍ በየትኛውም መስፈርት ቢታይ ዛሬን ብቻ በልቶ የማደር ለነገ ያለማለት የአህያዋ አይነት እሳቤ ነው። ይሄ ድርጊት እንዲቆም ከራስ አልፎ ለትውልድ የሚበቃ፣ ከዛም የራቀ ዓለም አቀፍ አስተሳሰብን መውረስ ያስፈልጋል።

ሙሰኞች በድርጊታቸው ብቻ አይደለም በባሕሪያቸውም ነውረኞች ናቸው። ሀገራቸውን ሊውጡ የተሰናዱ ደራጎኖች ናቸው። በሕዝብ ላብ፣ በወገን እንባ ራሳቸውን ፈጥረው ያሳደጉ፣ በሀገር ሀብት፣ በሕዝብ ጥሪት የራሳቸውን ሆድ ብቻ የሚሞሉ ስግብግቦች ናቸው። አረመኔነት መልክ ቢኖረው፣ አህያነት ስም ቢኖረው እነሱን ይሆን ነበር። እውነት ለመናገር ሙሰኞች በተግባራቸው እጅግ የዘቀጡ በሀገርና ሕዝብ ላይ ያመጹ ናቸው። ግብራቸው ከየትኛውም መጥፎ ነገር ጋር የማይነጻጸር ነው። በብዙ ነገራቸው ሀገራቸውን ጎድተዋል። ሥልጣናቸውን ተጠቅመው በሀገር ላይ ያደረሱት በደል እንዲህ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። እንዳውም በተግባራቸው የአህያን ያክል ግልጋሎት አልሰጡም። ከአሪት እስከ አዲስ ከዛም አልፎ እስከ አለንበት ጊዜ ድረስ አህያ በታማኝነት ስታገለግለን ኖራለች። ሙሰኞች ግን ከመስረቅና ከመዝረፍ የዘለለ ታሪክ የላቸውም፡፡

ሙሰኞች ሁልጊዜም አንድ ዓይነት ናቸው። አጋጣሚ ባገኙ ቁጥር ከመስረቅ ወደኋላ አይሉም። ለኢትዮጵያ እድገትና ብልጽግና ከለፉት ይልቅ ያጠፉት ይበልጣል። ‹እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል’ አለች አህያ የሚለው ተረት ሙሰኞችን በደንብ ስለሚገልጻቸው ‹እኛ ከሞትን ሀገር

ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ነፃ ሃሳብ

## “እኔ ከሞትኩ ሰርዶ...

> **ታማኝነት ኢትዮጵያን የማፍቀር ምልክት ነው። አንድን ሰው ከልባችን ስንወደው ነው እምነታችንን የምንሰጠው። እነኚህ ግለሰቦች ኢትዮጵያን ስለማይወዷት ሊታመኑላት አልቻሉም። ሕዝቡን ስለማያከብሩት በታማኝነት ሊያገለግሉት አልቻሉም**

ከ5ኛ ገጽ የዞረ

ትውደም’ አሉ ሙሰኞች በሚል ቢስተካከል ደስ ይለኛል። ምክንያቱም አሁን ላይ ለሀገራችን ጉስቁልናና ኋላቀርነት እየሠሩ ያሉት እነሱ ስለሆኑ። ራሳቸውን ለሀገር ሳይሆን ሀገርን ለራሳቸው አመቻችተው የተቀመጡ ናቸው። በትረ ሥልጣናቸውን ለሀገር ክብር አልተጠቀሙበትም። እየሰረቁና እያሰረቁ በሌብነት ሀሳብ ውስጥ ከድጡ ወደማጡ የሚዋዥቁ ናቸው። ለራሳቸው ባመቻቹዋት ሀገር ላይ፣ ለራሳቸው ባመቻቹት ማኅበረሰብ ላይ አዲስ ነገር መፍጠር አቅቷቸው እኩይ ድርጊታቸውን ለመሸፋፈንና በሌላው ላይ ለመላከክ የሚያደርጉት ድርጊታቸው ሌላ በመጥፎ የሚነሳ ግብራቸው ነው።

እነሱ ማለት የሀገርና የታሪክ የትውልድም ጠንቅ ናቸው። በሥልጣናቸው ተጠቅመውም በሙስና ተግባራቸው የሀገራችንን ተስፋ፣ የትውልዱን ደስታ እያበላሹ ነው። ዕውቀታቸው ተጀምሮ የሚያልቀው በመስረቅ ነው። ሌባ ለአመሉ ዳቦ ይልሳል እንዲሉ፤ ሁሌም በመስረቅ ተግባር ውስጥ ናቸው። እስኪበቃቸው ሰርቀው አልበቃቸውም። ወደፊት እንዴትና ምን እንደሚሰርቁ በማሰብ ከግብረአበሮቻቸው ጋር በመምከር ጊዜ የሚያጠፉ ናቸው። በዚህ በእነሱ ሀሳብ ውስጥ ኢትዮጵያ የለችም፤ በዚህ ሀሳባቸው ውስጥ ትውልድ አይገነባም። ይልቁንም ይሄ ሀሳብ የሀገርን ተስፋ የሚያደበዝዝ ጅምላ ጨራሽ መርዘኛ ሀሳብ ነው። ተባብረን ልናስቆመው ይገባል። የፀረ-ሙስና ኮሚሽንም ከወትሮው በተለየ መንገድ በዚህ ላይ መስራት አለበት። መንግሥትም የተለያ አመራር በመስጠት እንደነዚህ አይነቶቹን ሀገር ሻጪ ሌባና ባንዳዎች ሊቆጣጠር ይገባል።

ሙሰኞች ለሀገር በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ ናቸው። ሀገራችን በብዙ ችግር ተከባ ባለችበት በዚህና በዚያ ዘመን እነሱ ነበሩ። አሁንም ለሀገራችን ተጨማሪ ችግር ሆነው አሉ። መፍትሔ ሊያገኙ ይገባል። በብዙ ሀገራዊ ችግሮች ላይ ጆሮ ደግፍን የሚያክል ችግር ተጨምሮብን ይቅርና ወትሮም ኢኮኖሚያችን በመንገዳገድ ላይ ያለ ነን። እንኳንስ ዘንቦብሽ የሚለውን ታሪክ እየተረክን ዝም ማለት ሳይሆን ለችግሮቻችን መፍትሔ በመስጠት ላይ ማተኮር ይኖርብናል፡፡

ሀገር በሙሰኞች ስትበዘበዝ ማር የሌለው ቀፎ ናት። ሕዝብ ደግሞ ማር ይጠብቃል፤ ማሩ ግን ለሆዳቸው ባደሩ ስግብግቦች ይበላል። ሙሰኞችን ከወዲሁ አደብ ማስያዝ ካልተቻለም የሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ እንዲህ እየሆነ ነው። ማሩ ወደ ሕዝብ መድረስ አለበት። ባለሥልጣኖቻችን የማሩ ጠባቂ እንጂ ማሩን ቆርጠው የሚበሉና ወደቤታቸው ብቻ የሚወስዱ አይደሉም። የማሩ ባለቤት ሕዝብ ነው። ሕዝብ ባለሥልጣኖችን የሾመው የማሩ ቆራጭ ሆነው አብዝተውና አትረፍርፈው እንዲሰጡት እንጂ በውሸት ዜና ቀፏችን ማር አልያዘም ብለው እንዲያረዱት አይደለም፡፡

በታማኝ ባለሥልጣኖች ማር ያለበት ቀፎ ያስፈልገናል። ሀገራችን ማር ይዛ ሕዝቦች በጋራ እንዲበሉ የሚያስችል ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ያስፈልጋል። ማሯ በጥቂት ግለሰቦች የሚበላባት ሀገር ሊኖረን አይገባም። በታማኝነትና በቅንነት ሕዝብን ያስቀደመ አሠራር ያስፈልጋል። ሕዝብ አበባ እየተከለ፤ ለንቦች የሚመች ስፍራ እየፈጠረ ማሩ ግን በስግብግብ ሙሰኛ ባለስልጣን የሚቆረጥ መሆን የለበትም። ተቆርጦ ወደ ሕዝብ ቢደርስ ጥሩ ነው። እናም ሕዝብ ይቅደም፤ ሥልጣን ሕዝብ ማገልገያ ነውና፡፡

በሙሰኛ ባለስልጣኖች እንጀራ የሌለው ሌማት አንፈልግም። ባዶ ሌማት ምን ይሠራልናል? እንዲያበሉን እንጂ የሾምናቸው እንድናበላቸው አይደለም። ከድህነት እንዲያወጡን እንጂ በድህነታችን ላይ እንዲቆምሩ አይደለም። መስኮት አልባ ቤት ምን ያደርግልናል? እኛ የምንፈልገው በመተማመን ላይ የተመሠረተ ፖለቲካና ፖለቲከኛ ነው። አሠሪና ሠራተኛ ነው። ባለጉዳይና ባለሥልጣን ነው። ጥቂቶች ጠግበው ብዙኃኑ የተራበባት ሀገር ልትኖረን አይገባም። በእኔነት መንፈስ ተሰልበው ራሳቸውንና በዙሪያቸው ያሉን የሚጠቅሙ ሙሰኛ ጥቅመኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት ተጠያቂ እንዲሆኑ የሚያደርግ አሠራር ያስፈልጋል። ሀገራችን ከዚህ ውጪ የሚበጃት የለም። በኢትዮጵያ ተስፋ ላይ ለሚመጡ የማያዳግም እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል። ለሌላው ማስተማሪያ የሚሆን ፍርድ ያስፈልጋል። በእኛ ይብቃ.. እኛን ያየ ይቀጣ ብሎ የሚናገር ዘመን ተሻጋሪ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሊረቅ ይገባል።

በኢትዮጵያ ምድር የሙሰኞቻችን ግብር ከእንስሳ ግብር ያነሰ ነው። በዚህና በመሰለው ተግባራቸው ‹እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል’ አሉ ከማለት ውጪ ምን ሊባሉ ይችላሉ? በሥልጣን ስም እዛም እዚም የተሰገሰጉ እንስሳዊ ባሕሪን የሚያራምዱ ነውረኞች መታረም አለባቸው። ከትላንት እስከዛሬ በሙሰኞች የግፍ በትር ያልተመታ ኢትዮጵያዊ የለም። ዛሬም እንደትላንቱ ሀገራችን በነዚህ ግለሰቦች እየተቦጠቦጠች ነው። ይበቃል የሚል ድምጽ ከመንግሥትም ከእኛም ሊሰማ ይገባል፡፡

ታማኝነት ኢትዮጵያን የማፍቀር ምልክት ነው። አንድን ሰው ከልባችን ስንወደው ነው እምነታችንን የምንሰጠው። እነኚህ ግለሰቦች ኢትዮጵያን ስለማይወዷት ሊታመኑላት አልቻሉም። ሕዝቡን ስለማያከብሩት በታማኝነት ሊያገለግሉት አልቻሉም። ሀገራችን መታመንን በማያውቁ፣ ፍቅርን በማያውቁ ሌባና ራስወዳድ ባለስልጣናት ልትመራ አይገባትም። ከምንም በፊት ታማኝነትን መማር አለባቸው፤ መቀበልን ሳይሆን መስጠትን መልመድ አለባቸው፡፡

ሙሰኞች ኢትዮጵያን ቢወዷት ኖሮ በዚህ ልክ ባልጎዷት ነበር። ሕዝባቸውን ቢያከብሩት በዚህ ልክ ባልዋሹት ነበር። ኢትዮጵያ ለስግብግብ ባለስልጣናት ምንድን ናት? እንዴትም ብናየው ምንም አይደለችም። ጥቅማቸውን የሚያስጠብቁባት ሀገር እንጂ የሚሞቱላት እንዳይደለች ከእኩይ ከተግባራቸው መረዳት እንችላለን። የአውሬአዊ ማንነታቸው መደበቂያ እንጂ መድመቂያቸው አላደረጓትም። አዕምሮ የሚደምቀው ሀገርን ሲያደምቅ ነው። ማኅበረሰብን ሲያገለግል ነው። እነሱ ግን በሀገር ለመድመቅ እንጂ ሀገር በነሱ እንድትደምቅ አላደረጉም። ክብራቸውና ደስታቸው ሰርቆ በመብላት የሚመነዘር ነው። እውነትና ፍርሃት በነፍሳቸው ውስጥ የለም። እነዚህን ወንበዴዎች መታገል አለብን። መታገል ብቻ አይደለም እስኪወድቁ ድረስ፣ ዳግም መነሳት እስኪያቅታቸው ድረስ ልንታገላቸው ይገባል። ከነአስተሳሰባቸው፣ ከነሌብነታቸው፣ ከነድርጊታቸው እንዲቀበሩ ማድረግ አለብን፡፡

እኔ እስከማውቀው ድረስ የሀገር ፍቅር በተግባር ነው የሚገለጸው። ሀገር መውደድ ውስጥ እኔነት የለም። ሀገር መውደድ ውስጥ በጎ ሀሳብ እንጂ እንደ አህያ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል የሚል ፈሊጥ አይነገርም። ለሀገር የሚለፉ እነሱ የተባረኩ ናቸው። ለሀገር የሚለፉ አንድ ቀን በትውልዱ እንደሚከብሩ ስነግራችሁ ከልቤ ነው። አባቶቻችን ለሀገርና ለነጻነት በከፈሉት ዋጋ እያመሰገናቸው ነው። በዓድዋና በአንባላጌ፣ በካራማራና፣ በኦጋዴን ለሀገርና ለታሪካቸው ሲሉ በከፈሉት የሕይወት መስዋዕት ትውልድ እየዘከራቸው ነው። እንደ ሙሰኞች ያሉ በሀገርና በታሪክ ላይ መጥፎ አሻራ የሚያስቀምጡ እነሱ እነሱ ከኢትዮጵያ ማህጸን የሚፋቁበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም፡፡

ሀገር መልካም ነፍስ ትሻለች። ሀገር መልካም ልብ ግድ ይላታል። መልካም ነፍሶች ለሌላው የሚሆን ደስታ እንጂ ስቃይ የላቸውም። መልካም ልቦች ለሌሎች የሚሆን እውነት እንጂ ሐሰት አይኖራቸውም። አሁን ጊዜው በተባበረ ክንድ ኢትዮጵያን ወደ ፊት የምናሻግርበት ነው። ከእኔነት ወጥተን ወደ ሕዝባዊነት የምንሸጋገርበት የተሐድሶ ምዕራፍ ነው። አሁን ጊዜው እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል የምንልበት ሳይሆን በኔ መኖር ሌሎች እንዲኖሩ የምፈቅድበት ጊዜ ነው፡፡

አሁን ጊዜው በእኛ ፍቅር፣ በእኛ አንድነት፣ በእኛ ታማኝነት የልጆቻችንን ኢትዮጵያ የምንገነባበት እንጂ እንደ ሌባ ባለሥልጣን እየሰረቅንና እያሰረቅን በራስ ወዳድነት ሀገርና ታሪክ የምናወድምበት አይደለም። አሁን ጊዜው ለውጥ ከናፈቁ ሕዝቦች ጋር ወደ ፊት የምንልበት እንጂ ከሕዝብ የምንሰርቅበት አይደለም። ይሄ ጊዜ ከሌብነት አስተሳሰብ ተላቀን መልካም ሀገርና መልካም ትውልድ የምንገነባበት የመተማመን ጊዜ ነው። ይሄ ጊዜ ከመቼውም ጊዜ በላይ ኢትዮጵያን የምናገለግልበት፣ ሕዝባችንን የምንጠቅምበት የመነሳት ጊዜ እንጂ አጋጣሚዎች በተመቻቹልን ቁጥር የምንዋሽበት አይደለም፡፡

በሀገር ጉዳይ ላይ የድርሻችንን እንወጣ። በሀገር ጉዳይ ላይ ሁላችንም ያገባናል፤ መንግሥት ብቻ አይደለም፣ ሕዝብ ብቻ አይደለም፣ ጥቂት ለአገርና ሕዝብ የሚለፉት ባለስልጣናትም ጉዳይ ብቻ አይደለም። ሁላችንም ለሀገራችን ስፍራ አለን። በሀገር ጉዳይ ላይ የሚመለከተው የሚባል ነገር የለም። ሁላችንም ስለሀገራችን ይመለከተናል። ሁላችንም ስለሕዝባችን ያገባናል። ለሀገር ነቀርሳ የሆኑ ሙሰኞችንም የምንዋጋቸው በአንድነት ስሜት ነው፡፡

ማንም ይበለው ‹እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል.. አደገኛ አባባል ነው። ሀገር የሚያወድም..ትውልድ የሚመርዝ። ቃላት ምን ያክል ገላጭና ተጽዕኖ እንዳላቸው ለማወቅ ይሄን አባባል ማየቱ በቂ ነው። እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ግለሰብም ይሄን አባባል የሚሽር ሰብዕና ያስፈልገናል ባይ ነን። ምክንያቱም አሁን ላይ ሁላችንም ኢትዮጵያን በመፍጠር ሀሳብ ላይ ስለሆንን። አዲስ ሀገር በአዲስ አስተሳሰብ የምትፈጠር ናት። አዲስ ሀሳብ ከሌለን አዲስ ነገር አይኖረንም፣ የጥንቱን ስርዓት አራማጅ ነው የምንሆነው፡፡

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ‹‹ ስማርት ሲቲ›› - ለተቀላጠፈ አገልግሎትና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

የአለም የከተማ ነዋሪዎች ብዛት እየጨመረ መምጣቱንና ከዚህ ሕዝብ ግማሽ ያህሉ በከተማ እንደሚኖር መረጃዎች ይጠቁማሉ። በኢትዮጵያ 20 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ በከተማ እንደሚኖር እና እስከ 2040 ዓ.ም ድረስ የከተማ ሕዝብ ብዛት በሦስት እጥፍ ሊያድግ እንደሚችል መረጃዎች ያሳያሉ። እንደ አዲስ አበባ ባሉ ከተሞች ደግሞ የሕዝብ ቁጥሩ ከዚህም በላይ እንደሚጨምር ይገመታል።

በእዚሁ ልክ መንግስታዊና ሌሎች አገልግሎቶች መስጠት እንደሚያስፈልግ ይታመናል። ይሁንና የሀገራችንን ከተሞች ሁኔታ ብንመለከት በእዚህ በኩል ሰፊ ክፍተት ይታያል። ፈጣንና የተቀላጠፈ አገልግሎት በመስጠት በኩል ሰፊ ክፍተት ይስተዋላል። ሁኔታው በአግልግሎት አሰጣጥ፣ በአቅርቦትና ፍላጎት አማመጣጠን፣ ወዘተ ላይ በቴክኖሎጂ ታግዞ በትኩረት መስራትን ይጠይቃል። በዚህም ከተሞች ጫናዎችን እንዲቋቋሙ፣ ለኑሮ ምቹና ተስማሚ እንዲሆኑ በማድረግ የሚፈለገውን ለውጥ እንዲያመጡ መስራት ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ሆኗል። ለእዚህ ደግሞ ስማርት ሲቲ መገንባት ወሳኝ መሆኑ ታምኖበት እየተሰራ ነው፡፡

በሀገራችንም በአሁኑ ወቅት የዘመናዊ ከተማ /ስማርት ሲቲ/ ጉዳይ በስፋት እየተነሳ ይገኛል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአዲስ አበባና አደማ ከተሞች ስማርት ሲቲ የመገንባት ፍላጎት እና እንቅስቀሴዎች ይስተዋላሉ። ለመሆኑ ስማርት ሲቲ መገንባት ለምን አስፈለገ? እንዴትስ እውን ሊሆን ይችላል?

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ስማርት ሲቲ የመገንባት ጽንስ ሀሳብ ዘመኑ የሚጠይቀውንና ከዘመኑ ጋር አብሮ የሚሄደውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ዘመናዊ የአሠራር ሥርዓትን መዘርጋትን ይጠይቃል። በከተሞች ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ መረጃዎች (ዳታ) ላይ ተመሥርቶ በመተንተን የሞባይል መተግበሪያዎች በመጠቀም የከተማ ኢንቨስትመንት አማራጮች፣ የቱሪዝም መዳረሻዎች፣ የከተማ የመሬት አስተዳደር እንዲሁም በቴክኖሎጂ የታገዘ የትራፊክ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋትንም ይፈልጋል። ከተሞች ሲዘመኑ ለነዋሪዎቻቸው ምቹ ፤ ለኢንቪስትመንት ተመራጭና እድገታቸው ፈጣን ስለሚሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪና ተመራጭ ይሆናሉ ።

በአዲስ አበባ ከተማ የስማርት ሲቲ ትግበራ ወሳኝ መሆኑ እየተገለጸ ነው። ከተማዋ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ፣ የአፍሪካ መዲና ከመሆኗም ባሻገር የዓለም አቀፍ ተቋማት የአፍሪካ ቅርንጫፎችና የሀገራት አምባሲዎች መቀመጫ እንደ መሆኗ ነዋሪዎቿን፣ እንግዶቿን፣ እድገቷን፣ ወዘተ. ታሳቢ ያደረገ ከተማዋን የማዘመን ስራ ውስጥ መግባት ያስፈልጋል።

**አዲስ አበባ ከተማን ስማርት ሲቲ ለማድረግ ጥናቶች ቀርበው ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎባቸዋል። በዚህም የቴክኖሎጂ ፈላጊ ተቋማትና የቴክኖሎጂ አመንጪ ተቋማት ተገናኝተዋል፡፡ ለከተማዋ የሚያስፈልጉ ቴክኖሎጂዎች በመምረጥ በመለየት ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ገልጸዋል**

የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ በአዲስ አበባ በሚተገበረው የስማርት ሲቲ ፕሮጀክት ላይ እንዳሉት ፤ በአዲስ አበባ ከተማ የስማርቲ ሲቲ ግንባታ እንደሚያስፈልግ ታምኖበት እየተሰራ ነው። እየጨመረ የሚመጣውን የከተማዋን ነዋሪዎች ብዛትና ፍላጎት ለማሟላት ውብ፣ ሳቢና ለሰው ልጆች ቀላል የሆነ ዘመናዊ ከተማ ለመገንባት የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል። አዲስ አበባ ከተማን በማዘመን ለነዋሪዎቿ ምቹ፣ ለኢንቨስትመንት ተስማሚና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ ከተማ ለማድረግ የሚያስችል የቅድመ ትግበራ ስራ ሲሰራ ቆይቷል። አዲስ አበባን ዘመናዊ ከተማ / ስማርት ሲቲ / በማድረግ የከተማዋን ነዋሪዎች እንግልት በማስቀረት ቀልጣፋ የሆነ አገልግሎት መስጠት ቅድሚያ የተሰጠው ተግባር ነው።

እሳቸው እንደሚሉት፤ በከተሞች በከፍተኛ ፍጥነት ቁጥሩ እየጨመረ ያለውን ነዋሪ ፍላጎት ለማርካት ውብ፣ ሳቢ እንዲሁም ለሰው ልጆች ቀላልና ምቹ የሆኑ ዘመናዊ ከተሞችን ለመገንባት የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት ጊዜ ሊሰጠው አይገባም። በዚህ ረገድ በአዲስ አበባም ዘመናዊ ከተማን / ስማርት ሲቲ/ የመገንባት ጽንስ ሀሳብ ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት አስፈላጊ በጀትም ተመድቦለት በጥናት ተደግፎ፣ ለስኬቱ ተቋማዊ አደረጃጀቶችን በማዋቀር አስፈላጊውን የሰው ኃይል በማደራጀት ዘርፉ ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ እየተሰራ ይገኛል።

ቴክኖሎጂዎች ከፈጠራና ከሰዎች ጋር የተቆራኙ መሆናቸውን ጠቁመው፤ ቴክኖሎጂ ልናሳካ የሰብነውን ራዕይ መተግበሪያ መሳሪያ፣ ከተሞች ደግሞ የመተግበሪያ ስፍራዎች ናቸው ሲሉ አብራርተዋል። ቴክኖሎጂ ለአንድ ሀገር ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት አይነተኛ ሚና ሊጫወት የሚችለው ህብረተሰቡ ዘንድ ሲሰርጽና በፈጠራ ሲታገዝ ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ ከቴክኖሎጂ አኳያ ያሉት መሰረተ ልማቶች ወይም ቴክኖሎጂዎች በግዥም ሆነ በምርምር የሚገኝ የቴክኖሎጂ እውቀትን ለማሰባሰብ ፣ ለማከማቸትና ለማስራጨት የሚያስችሉ ካለመሆነባቸው ጋር በተያያዘ በሀገሪቱ የቴክኖሎጂ እውቀት ለማከማቸትም ሆነ የተከማቸውን እውቀት በሚገባ ጥቅም ላይ መዋል የሚያስችል ሁኔታ እንደሌለ ይገልጻሉ። በስራ ላይ ያሉት ቴክኖሎጂዎችም ቢሆኑ የተመቻቹ ናቸው የሚባሉ አይነቶች አንዳልሆኑ ጠቁመዋል።

ከንቲባዋ እንዳብራሩት፤ ከተሞች በዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች አገልግሎታቸውን ማሳለጥ እንዲችሉ በቅድሚያ ከአካበቢው ጋር የተጣጠመና የተቀናጀ የቴክኖሎጂ መሠረተ ልማት መዘርጋትና ለዚህ የሚመጥን ቴክኖሎጂን መመረጥ ያስፈልጋል። በተለይም ውብ ከተሞች በመፍጠር ዘላቂነታቸውን ለማረጋገጥ ቴክኖሎጂ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው።

የሰማርት ሲቲ ለሕዝቡ አዳዲስ እድሎችን፣ የተሻለና ቀልጣፋ አገልግሎት፣ የነዋሪዎችን የደህንነት ሁኔታ ለማረጋገጥ ያስችላል ያሉት ከንቲባዋ፣ ወጪንም ይቀንሳል፣ በመንግሥትና በከተማ ነዋሪዎች መካከል ያለውን እምነት ብሎም ትብብርን ያሳድጋል ይላሉ።

ከንቲባዋ የሕዝብ እንግልትን ለማቅለል ያስችል ዘንድ አገልግሎት አሰጣጥን ለማዘመን እየተሰራ ነው ብለዋል። ከተማን ማዘመን ሁሉንም ነገር በአንድ ጊዜ ከታች ለመጀመር ሳይሆን ያሉንን መሠረተ ልማቶች መነሻ በማድረግ መሻሻል ያለባቸውን ማሻሻል እንዲሁም በአዲስ መልክ መገንባት ያለባቸውን መገንባት ውጤታማ ሥራ መሥራት የሚያስችል መነሻ ሀሳብ ነው ሲሉ ከንቲባዋ አመልክተዋል። በስራ ላይ ያሉ የቴክኖሎጂ አገልግሎቶች ሳይቋረጡ አዳዲስ አሠራሮችን በመዘርጋት የማሸጋገር ሥራዎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ለማድረግ በትኩረት መስራት እንደሚገባ ተናግረዋል። ከተማን የማዘመን አሠራር ጊዜ የሚፈልግና በሂደት የሚፈጸም መሆኑንም ተናግረው፣ ሁሉንም ዘርፎች በአንድ ጊዜ ወደ ዘመናዊ አሠራር ማስገባት እንደሚቻል አስታውቀዋል።

አዲስ አበባን ለነዋሪዎቿ ምቹና ተስማሚ ለማድረግ የተጀመረው ዘመናዊ ከተማን የመገንባት /የስማርት ሲቲ/ ፕሮጀክትን ተቋማት ወይም አመራሮች ብቻቸውን የሚፈጽሙት እንዳልሆነም ጠቁመው፣ የሁሉንም ቅንጅት እንደሚጠይቅ አስታውቀዋል። እንደ ስሟ አበባ የሆነች ዘመናዊ አዲስ አበባን የመገንባት ሥራዎችን በማቀላጠፍ ቀላልና ምቹ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ለመተግበር የተጀመረውን ስራ አጠናክረን እንቀጥላለን ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የአዲስ አበባ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ቴክኖሎጂ ልማት ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሀቢባ ሲራጅ እንዳሉት ከተማዋን ዘመናዊና ቀልጣፋ አገልግሎት አሰጣጥ ያለባት፣ በኢኮኖሚ የዳበረች፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የበለፀገችና ለነዋሪዎቿ ምቹ የሆነች ለማድረግ ይሰራል። በከተማዋ የዲጂታል አገልግሎት ለመዘርጋት ከ2 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር በላይ በመመደብ ለኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ /አይሲቲ/ግንባታ፣ የተቀናጀ የሶፍትዌርና ሌሎች ፕሮጀክቶችን ለመገንባት እየተሰራ ነው።

የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዲጅታል ኢኮኖሚውን የሚመራ መሳሪያ እንዲሆን ለማድረግ እየተሰራ መሆኑን የሚገልጹት ወይዘሮ ሀቢባ፤ ባለፉት ዓመታት የሶፍት ዌር ፕሮጀክቶችን በልማትና የተቀናጀ የኔትወርክ መሠረተ ልማት ፕሮጀክቶችን በማጠናከር ተቋማት የቴክኖሎጂ ልማት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል። ዘንድሮም የተለያዩ ፕሮጀክቶች ተቀርጸው ወደ ሥራ እንዲገቡ ለማድረግና አገልግሎቶችን ለማዘመን ሰፋፊ ሥራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኙ ጠቁመዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ በትምህርት ቤቶች፣ በወሳኝ ኩነት ቢሮዎች፣ በቴክኒክና ሙያ ተቋማት፣ በትራፊክ ማኔጅመንት ፣ በጤናና በሌሎች ተቋማት ቴክኖሎጂን በመጠቀም አገልግሎትን በማቀላጠፍ የተጀመረውን ዘመናዊ ከተማ ግንባታ በዲጂታል ቴክኖሎጂ ለማሳደግ በትኩረት እየተሰራ ነው። በአዲስ አበባ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፣ በአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ፣ በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር፣ በኢትዮ ቴሌኮም ዘርፍ ከተማዋን ስማርት ለማድረግ ጥናቶች ቀርበው ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት ተደርጎባቸዋል።በዚህም የቴክኖሎጂ ፈላጊ ተቋማትና የቴክኖሎጂ አመንጪ ተቋማት ተገናኝተዋል። ለከተማዋ የሚያስፈልጉ ቴክኖሎጂዎች በመምረጥ በመለየት ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የከተማ መሠረተ ልማት ሚኒስቴር የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ አቶ ኢትዮጵያ በዴቻ በበኩላቸው ከተሞችን የማዘመን ስራ በከተሞች የሚሰጡ አገልግሎቶችን ተደራሽ ለማድረግ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች እና አሠራሮችን ተግባራዊ በማድረግ የተሻሉ አገልግሎቶች መስጠትን ታሳቢ እንደሚያደርግ ይገልጻሉ፡፡

አቶ ኢትዮጵያ እንዳሉት፤ ዘመናዊ ከተማን/ስማርት ሲቲ/ የመገንባት ጽንሰ ሀሳብ በዓለም ሀገራት በተሻለ ቴክኖሎጂ በተሻለ አሠራር ከተሞችን በማዘመን ከተሞችን ለነዋሪዎቹ የተሻለ አድርጎ ማቅረብ የሚሉትን ያካትታል። ይሄም ከተሞች በሚፈለገው ስታንዳርድ መሠረት በፕላን እንዲመሩ ማድረግ ያስችላል። በፕላን የሚመሩ ከተሞች ደግሞ በከተማ ለሚኖረው ሕዝብ የሚፈለገውን አገልግሎት በተቀላጠፈ መንገድ፣ በተሻለ አረዳድ ለመስጠት ያስችላል፡፡

ከተሞችን በፕላን መምራት ዘመናዊ ከተማን ለመገንባት ትልቅ እድል እንደሚፈጥር አቶ ኢትዮጵያ ጠቅሰው፣ ከተሞችን ማራኪ ማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግቶ፣ ቴክኖሎጂዎችን በማላመድ፣ ባለው የሰው ኃይል ተጠቅሞ አገልግሎትን ማዘመን እንደሚቻል ይገልጻሉ።

እሳቸው እንዳሉት፤ ከተሞችን በቴክኖሎጂ ማበልጸግ የትራንስፖርት አገልግሎትን ማሳለጥ፣ ኢንተርኔትን ተደራሽ ማድረግ እና የኤሌክትሮኒክስ ዘዴዎችን ተጠቅሞ አገልግሎቶችን ማቀላጠፍ እና የመሳሰሉት ሂደቶች ከተማን ለማዘመን ወይም ዘመናዊ ከተማን/ ስማርት ሲቲ/ ለመገንባት ለሚደረገው ጉዞ እንደ መነሻ ናቸው። የተሳለጠ የትራንስፖርት አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ፣ የአካባቢውን አየር ለመቆጣጠር የራስን ድርሻ ማበርከት፣ ሕብረተሰቡ በቀላሉ አገልግሎቱን ማግኘት እና ፈጣንና ጊዜ ቆጣቢ ዘዴዎች መጠቀም የሚችልበት ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ነው ።

አቶ ኢትዮጵያ እንዳሉት፤ ዘመናዊ ከተማ/ስማርት ሲቲ/ መገንባትን በተመለከተ ትኩረት በማድረግ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራዎች እየተሰሩ ናቸው። ለተግባራዊነቱም ልዩ ትኩረት እንዲሰጥ በማድረግ የሕግ ማዕቀፎች እንዲዘጋጁ ፣የተለያዩ ሀገራትን ተሞክሮዎች የመቀመር እና የመሳሰሉት በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡

ከተሞችን በማዘመኑ ሂደት ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲና አዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም ሌሎች የትምህርት ተቋማትም ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረጉ ስልጠናዎች እንደሚሰጡ ጠቅሰው፤ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ከተቋማቱ ጋር በትብብርና በቅንጅት እየሰራ እንደሚገኝ ይናገራሉ፡፡

የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያው አቶ ሀብታሙ ዳምጤ እንደሚሉት፤ ከተሞችን ዘመናዊ ማድረግ/ የስማርት ሲቲ/ ጽንስ ሀሳብ ለኢትዮጵያ ከተሞች ያስፈልጋል። ከተማ ሲዘመን እንደ ሀገር በቴክኖሎጂ ወደኋላ ለተቀረበት ምክንያት የሆኑ ችግሮች መቅረፍ ይቻላል። ከዓለም ሀገራት ጋር ተወዳዳሪ ለመሆን ይጠቅማል፡፡

አሁን ላይ አለምን እየተቆጣጠሩ ያሉት እንደ ፌስ ቡክ፣ ዩቲዩብ ያሉት የሶሻል ሚዲያዎችን በመጠቀም የውጭ ምንዛሬን ማግኘት ያስችላል። ለአብነት ሕንድ 30 በመቶ የሚሆነውን የውጭ ምንዛሬ ገቢ የምታገኘው ከዩቲዩብ ነው። በዚህ ላይ ከሶፍትዌር ሽያጭ የምታገኘው ሲጨመር 40 በመቶ ያህል ይሆናል።

እኛ እንደ ሀገር የውጭ ምንዛሬ ገቢ ለማግኘት ከምንልካቸው ምርቶች ባሻገር ባለው የሰው ኃይል ላይ ብንሰራ በቀላሉ ተጠቃሚ መሆን እንችላለን ያሉት ባለሙያው፣ ይህ ዘመናዊ ከተማን /የስማርት ሲቲን/ የመገንባቱ ሀሳብ አንድ እርምጃ ከፍ የሚያደርግ ነው ይላሉ፡፡

እንደ አቶ ሀብታሙ ገለጻ፤ ዘመናዊ ከተማ የመገንባት ጽንሰ ሀሳብ ኢንፎርሜሽን ፣ቴክኖሎጂና ኮሙኒኬሽን አንድ ላይ አጣምሮ በመያዝ መንግሥትና ሕዝብ ይበልጥ የሚግባቡትን ሁኔታ ለመፍጠር ይጠቅማል። በአጠቃላይ ዘመናዊ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች መጠቀም ያስችላል ።

በሀገሪቱ ተግባራዊ እየሆነ ያለው በብሔራዊ ዲጅታል መታወቂያም የከተማን ማዘመን አንድ አካል ነው ያሉት አቶ ሀብታሙ፤ አስፈላጊዎቹ መረጃዎች አንድ ቦታ ላይ ተሰብሰበው ከተቀመጡ ነገ ዘመናዊ ከተማ ሲገነባ ከዜሮ እንደማይጀመርና መረጃው ከዚያ የሚወሰድበት ሁኔታ እንደሚኖር አመላክተዋል። እነዚህ ቴክኖሎጂዎች በዲጅታል ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም አገልግሎትን በቀላሉ እንዲያገኙ የሚያስችሉ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ የህብረተሰቡን እንግልት በመቀነስ ትልቅ ሚና እንዳላቸው አስታውቀዋል። በአዲስ አበባ እየተተገበረ ያለው የዘመናዊ ከተማ/ ስማርት ሲቲ ግንባታ ዘመናዊ ከተማ የመገንባቱን ሂደት አንድ እርምጃ ወደፊት ያስኬዳል ይላሉ።

ዘመናዊ ከተማ ለመገንባት የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶችን የማሟላቱ ሥራ በጥሩ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ የሚገልጹት አቶ ሀብታሙ፤ አሁን ላይ ያለን አቅም ተጠቅሞ በቴክኖሎጂ በመታገዝ ከተሰራ ዘመናዊ ከተማ የመገንባቱን ስራ ቀላል እንደሚያደርገው ጠቁመዋል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የፖለቲካ ገበያው ስጋትና መፍትሄዎች

**አስመረት ብስራት**

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐብይ አህመድ የብልፅግና ፓርቲ ባካሄደው የማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ላይ የፖለቲካ ገበያ በኢትዮጵያ በዝቷል ። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ገበያ ከጊዜ ወደ ጊዜ መልኩን እየቀየረ የብልፅግና ጉዞውን አደጋ ውስጥ የሚከት ልምምድ ምኅዳሩን ወሮታል ሲሉ መናገራቸው ይታወሳል።

የፖለቲካ ገበያ ማለት ምን ማለት ነው? የፖለቲካ ገበያ ፅንስ ሀሳብ መነሻው ከየት ነው? በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ እንዴት ይገለፃል? ስንል ከፖለቲካ ምሁራን ጋር ቆይታ አድርገናል።

የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ዋና እንባ ጠባቂ ዶክተር እንዳለ ሀይሌ እንዳሉት፤ የፖለቲካ ገበያ ጽንሰ ሐሳብን ያመነጨው ፕሮፌሰር አሌክስ ዴዋል ነው። ፕሮፌሰር አሌክስ ዴዋል ኢትዮጵያን ጨምሮ የአብዛኞቹ የአፍሪካ ቀንድ አገሮች ፖለቲካን ጠንቅቆ ያጠና ተማራማሪ ነው። በቀድሞዋ ሱዳን የነበረውን ግጭት በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ከተወከሉ ልሂቃን መካከል አንዱ ነበር ።

ጠቅላይ ሚንስትሩ የፖለቲካ ገበያ መስፋት አለበት የሚል ሀሳብ ሲያነሱ ነበር። አንዳንዶች እንደሚሉት የፖለቲካ ገበያ በግላዊ የፖለቲካ ግብይት ላይ የተመሠረተ የአስተዳደር ሥርዓት ሲሆን፣ የፖለቲካ አገልግሎት በጥቅማ ጥቅም ወይም በዝምድና ላይ የተመሰረተ ሊሆን ይችላል። ይህን መሰባሰብ ወይንም በጥቅም መተሳሰርን የሚፈጥሩት ድምፅ ለማግኘት፤ በስልጣን ላይ ያላቸውን እድሜ ለማርዘም ሊሆን እንደሚችል ይናገራሉ።

የፖለቲካ ገበያ መስፋት አለበት ሲባልም ከገበያ የሚገዛው የመንግስት ወይም የብልጽግና ሃሳብ ብቻ አይደለም ።የሁሉም ሃሳብ የብልጽግናን ጨምሮ ወደ ገበያ ይወጣል ከዚያ ህዝብ ገዥውን ሃሳብ ከገበያ ይሸምታል። ዴሞክራሲ የሚያድገውም በመሳሪያ ወይም በጡንቻ ሳይሆን በሃሳብ የበላይነት ነው ለማለት እንደሆነ ያስረዳሉ።

ሌላው የድሬደዋ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስና አለም አቀፍ ግንኙነት መምህርና ተመራማሪ አቶ ሱራፌል ጌታሁን ፤ የፖለቲካ ገበያ በብሔር ወይም በሃይማኖት ማንነት ላይ ተሞርኩዞ አቅም የሌላቸውን ሰዎች ሰብስቦ እዛው መተሻሸት ሲሆን ሌላው ደግሞ ፕሮፌሰር አሌክስ ደዋል "ፖለቲካል ቢዝነስ ኢን አፍሪካ" ብሎ የፃፈው ሀሳብ ላይ እንደተመላከተው፣ ግጭት የፖለቲካ ገበያው ስራ ፈጣሪ ወይም ኢንተር ፕሪነር ነው ይላል።

እሱ እንደሚለው ዳርፉር ላይ አደራዳሪ የነበረው የኳታር መንግስት ነበር። በወቅቱ የአሜሪካው መከላከያ ሚኒስቴር ሮበርት ጌጅ ነበሩ። አቡጃ ላይ በዚሁ በዳርፉር ግጭት ላይ ሰብስባ ያደርጋሉ። እና በወቅቱ የዳርፉር ተደራዳሪዎች ከስብሰባው ወጥተው ደውለው በ30 ሚሊየን ዶላር እንስማማ ወይ ሲባባሉ መሰማቱን ይጠቅሳል ። ግጭቱን ለማስቆም ሰላሳ ሚለየን ዶላር መጠየቃቸው ግጭት ለፖለቲካ ገበያው ምቹ መሆኑን ማሳያ እንደሆነ ይናገራሉ።

አሁን በሀገራችን ያለው ሁኔታ በሁለት አይነት መንገድ ይገለፃል። አንዱ የውጭ ሀይሎች ናቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የብሄር ፖለቲካንና ብሄር አቀንቃኞችና አማፂዎች፣ የታጠቁ ሀይሎች የራሳቸውን ፍላጎት ለማሳካት ፖለቲካውን ለግብይት የሚጠቀሙበት ሁኔታ አለ። በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ አካላት አሉ፤ ያንን ግጭት መተደደሪያቸው አድርገው የሚኖሩ። ሀገሪቱ ውስጥ ሰላም በመኖሩ ጥቅም እናጣለን ብለው የሚያስቡም አይታጡም።

አለምአቀፍ ተቋማትና ጂኦ ፖለቲክስ ውድድር ላይ ያሉ ሀገራት አሉ። ግጭት በተራዘመ ቁጥር በግጭት ውስጥ ገብተው የራሳቸውን ጥቅምና ፍላጎት ለማስጠበቅ የሚሯሯጡበት ሁኔታ አለ። ሀገሪቱ ውስጥ ያለውን ሁኔታ እንደ መልካም አጋጣሚ የሚጠቀሙ አካላት አሉ። ይህም ነው ሊብራሊዝም የሚለው ፅንሰ ሀሳብ የበዛ ነፃነትን ሰጥቶ በነፃነት ስም ታዳጊ ሀገሮች ላይ ግጭት መነገጃ ነው ያደረጉት። የፖለቲካ ንግዱም እንዳይቋረጥ እንደኛ ሀገር አይነት የብሄር ብሄረሰብ ስብጥር ያለበት ሀገር ላይ በገንዘብም በሀሰት ፕሮፖጋንዳም ግጭት እንዳይቆም በማድረግ ለእነሱ ገበያ ምቹ የሆነን ደሴት ይፈጥራሉ።

> **የፖለቲካ ገበያ የሚፈጠረው ሰላም በሌለበት ሀገር ነው ። ለምን ሰላም በሌለበት ሀገር የፖለቲካ ገበያው ይፈጠራል ቢባል ሀገር ውስጥ ያሉ ተቋማት የትኩረት አቅጣጫቸው ወደ ጦርነቱ ስለሚሆን፤ መንግስቱም ሙሉ ሀይሉን ሰላም ወደ ማስከበሩ ስለሚያደርግ ነው**

የፖለቲካ ገበያ ከፓርቲ መዋቅር እስከ አለምአቀፋዊ ይዘት ያለው፤ የማይታይ እጅ የምንለው አይነት ለሀገሪቱ ከባድ ፈተና የሚሆን ጉዳይ ነው። ዲሞክራሲያዊ ተቋማትም እናዳይገነቡ አንዱ መሰናክል ይሄ የፖለቲካ ገበያ ባልተገባ መልኩ መሄዱ እንደሆነ ይናገራሉ። በሀገሪቱ ሰላም መስፈኑ የሚያሳስባቸው አካላት በህገወጥ የገንዘብና የመሳሪያ ዝውውር ላይ ተሰማርተው የነበሩ ሰዎች ግጭቱ እንዳይቆም የተቻላቸውን ሁሉ ያደርጋሉ።

የፖለቲካ ገበያ በተለይም አፍሪካ ቀንድ ላይ ሱዳንና ደቡብ ሱዳን ላይ የነበረ ግጭት በዋናነት አሜሪካና አውሮፓ የነበሩ የሱዳን አማፂ ቡድን ገንዘብ፤ የራሱን ወገኖችንና ደጋፊዎቹን በመሰብሰብ ግጭት የማስቆምም ሆነ የማስቀጠል ስልጣንን የራሱ ያደርገው እንደነበረ አቶ ሱራፌል ጠቅሰዋል።

የአምቦ ዩኒቨርሲት የፖለቲካ ሳይንስ መምህር አቶ ሰለሞን ተፈራ ።የፖለቲካ ገበያ የምንለው አንድ ሰው በሀሳብ በችሎታ ሳይሆን በገንዘብ ስልጣን ይገዛል። ከዛ በኋላ ደግሞ ስልጣን ላይ ለመቆየት ለሱ ፕሮፖጋንዳ የሚሰሩ ኔትወርክ ይገዛል። የዚህ አካል ተባባሪ ሆነው የተጋመዱት ኔትወርክ ውስጥ ያሉት ሰዎች ለሰባሰባቸው ባለስልጣንም ታማኝ ናቸው። እነዚህ አገልጋዮች ታማኝ እንዲሆኑ ባለስልጣኑ ለኔትወርኩ የሚያገለገሉትን ሰዎች በዘመድ አዝማድ ወይም ፓትሮሊያንዚም በሚባለው ሁኔታ ትስስር ይፈጥራል። ይህን የጥቅም ትስስር ደግሞ የፖለቲካ ገበያ እንለዋለን።

ይህ ሀገራችን ውስጥ እንዴት መጣ? ይህ የፖለቲካ ገበያ የሚያስከትለውን ጉዳትስ እንዴት መከላከል ይቻላል? ለሚለው ጥያቄ መልስ የሚሆነው በተለይ ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ገበያ(ፖለቲካ ማርኬት ፕሌስ) በቅርብ ጊዜ ቃሉ ገኖ ቢሰማም ባለፉት አርባ አመታት በዚህ የፖለቲካ ስርአት ውስጥ የነበረ መሆኑን ያስታውሳሉ።

ይሄ እንዴት መጣ ብለህ ስጠይቅ አንደኛ የመንግስታት ወደ ስልጣን አመጣጥ እንዴት ነበር ብሎ ማየት ወሳኝ መሆኑን ይናገራሉ።ለምሳሌ አንድ መንግስት ወደ ስልጣን ሲመጣ ለጊዜው የተለያዩ ተቋማትን ያቋቁማል ፤ ህጎችንና ደንቦችንም ያወጣል። እነዚህ ሲወጡ ግን ያወጣው አካል በትክክል ይጠቀምበታል ወይ ተብሎ ሲታይ ግን ተግባራዊነቱ አይታይም።

ህጉን የሚያወጡትም ጊዜ መግዣ የፖለቲካ አካሄዱን በአግባቡ እስከሚገነዘቡ መቆያ ነው። ብዙ ጊዜ በትጥቅ ትግል ወደ ስልጣን የመጡ ሀይሎች" እኛ ዋጋ ስለከፈልን እኛ መምራት አለብን" የሚል ነገር ሲያነሱ ይሰማል። ይህ ሀሳባቸው የፀና እንዲሆን በተለያዩ ሁኔታዎች ትስስርን ይፈጥራሉ። እነሱ የሚያምኑት በአቋቋሚቸው ተቋማትና ባወጣቸው ህጎች ከመተዳደር ይልቅ መደበኛ ያልሆኑ ህጎቻቸውን ይከተላሉ። በዚህም ሰው አስተሳሰቡ ሳይሆን ማንነቱ ብቻ እየታየ ወደስልጣን የሚጋበዝበት ወይም ከስልጣን እንዲወገድ የሚደረግበት አሰራርም የፖለቲካ ገበያው አካል ነው።

ሰው ማንነቱ ከታየ ደግሞ ምንም አይነት የበሰለ ሀሳብ ቢኖረው የመጣበት መሰረት ለስልጣን ከማይፈለጉት ውጪ ከሆነ በዚህ ምክንያት ብቻ ሲወገድ ይታያል። ሌላው የገዥው ፓርቲ ባህሪ ይታያል። ለምሳሌ አንድ ጨቋኝ የሆነ ስርአት ያለው የበላይነቱን የሚያሳይ ፓርቲ ወይም የሶሻሊዝም ሪዮተ አለም የሚከተል ፓርቲ ለዚህ አይነት የፖለቲካል ማርኬት ምቹ የሆኑ ቦታዎች ናቸው። ለምሳሌ ሀገራችን ውስጥ ያሉ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ሊቀመንበርና ፀሃፊ ይኖርና አባል የላቸውም። ጉባኤ ጥሩ ሲባሉ አባላትን የሚከራዩበት ሁኔታ አለ። በገንዘብ ይገዛሉ ማለት ነው። ይሄንንም እኔ በምሰራው ምርምር ውስጥ በተጨባጭ ያየሁት ነው።

ሌላው በኢትዮጵያ ሀገረ መንግስት ግንባታ ጠንካራ አለመሆን ለፖለቲካ ገበያነት ምቹ መደላድለ ፈጥሯል። የሀገረ መንግስት ግንባታ ማለት የተቋማት ግንባታ ማለት ነው። የፍትህ ተቋማት ፤ የኢኮኖሚ ተቋማት ፤ የህግ አስከባሪ ተቋማት ግንባታ በጣም ደካማ ስለሆነ ነው። የሀገር ግንባታ ወይም ኔሽን ቢዩልዲንግ የሚባለው በኢትዮጵያ ውስጥ በጣም አከራካሪ ሁኔታ ላይ ነው ያለው። የሀገሪቱ ህዝብ ያለው አስተሳሰብ ግንባታ ወይም የአእምሮ ግንባታ በአንድ የተቃኘ አይደለም ።

አንዳንዱ እኔ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም በማለት ብሄሩን ይገልፃል። አንዳንዱ ደግሞ እኔ ኦሮሞ ነኝ፤ አማራ ነኝ፤ ቅማንት ነኝ፤ ትግሬ ነኝ ሲል ይሰማል። ይሄ ከምን መጣ ስንል የሀገሪቱ የሀገር ግንባታ በማንነት ያለመስማማት ነገር ይታያል። ይህም ደግሞ ሌሎች በመካከል ብጥብጥን ፈጥሮ ለፖለቲካ ገበያው ምቹ ለማድረግ ለሚሰሩ ሰዎችም የተመቸ ይሆናል።

በሀገሪቱ ውስጥ እያንዳንዱ የፖለቲካ አካሄድ በገበያ ወይም በጥቅም አይን ነው የሚታየው። አንድ ሰው ስልጣን ሲይዝ "እንኳን አለፈለት" ነው የሚባለው። ለሀገሪቱ የሚጠቀም ሰው ወደ ስልጣን መጣ ሲባል አይሰማ። አንድ ሰው ስልጣን መያዙ የመጨረሻ ግቡ እራሱን በኢኮኖሚ ለማሻሻል እንጂ ሀገርን ለማገልገል አይደለም። የፖለቲካ ገበያ አለ ማለትም ፍትሃዊ ያልሆነ የሀብት ክፍፍልን ያመጣል።

የፖለቲካ ገበያ የሚፈጠረው ሰላም በሌለበት ሀገር ነው ። ለምን ሰላም በሌለበት ሀገር የፖለቲካ ገበያው ይፈጠራል ቢባል ሀገር ውስጥ ያሉ ተቋማት የትኩረት አቅጣጫቸው ወደ ጦርነቱ ስለሚሆን፤ መንግስቱም ሙሉ ሀይሉን ሰላም ወደ ማስከበሩ ስለሚያደርግ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትሩም ይሄንን ያነሱበት ምክንያትም ባለስልጣናት ምቹ አጋጣሚዎችን ተጠቅመው የፖለቲካ ገበያውን አሳሳቢ ደረጃ መድረሱን ስለተመለከቱ ነው ይላሉ።

ዋና እንባ ጠባቂ ዶክተር እንዳለ መፍትሄ ሀሳብ ሲያስቀምጡ በፖለቲካ ገበያ ሁሉም ሀሳብን በሀሳብ መሞገት መለመድ አለበት። መንግስት እንደ ግለስብ ማሰብ ያለበትም ሆደ ሰፊ እና ታጋሽ መሆን አለበት። ይህ ሲባል የዜጎችን መብት መደፍጠጥ መብቱ ነው ማለት አይደለም ።

አቶ ሱራፌል የመፍትሄ ሀሳብ ብለው ያነሱት፤ ከዘህ አይነት ችግር ውስጥ ለመውጣት መንግስት ዲሞክራሲያዊ የሆነ ሲስተምን መዘርጋት ሲችል ነው ። ሌላው ጠንካራ ተቋማትን መገንባት ሲሆን በግለሰቦች የዝምድና ትስስር የሚያዝ ስልጣንም ሆነ ሀብት ያለበትን የተጋመደ ሰንሰለት በመበጣጠስ በግለስቦች ችሎታና እቅም ላይ ብቻ የተመሰረቱ ጠንካራ ተቋማትን መመስረት ያስፈልጋል። ሶስተኛው ደግሞ በኢኮኖሚ ውስጥ ያሉት ባለሀብቶች የመንግስት ተቋማትን በረጅም እጃቸው ሀሳብ እንዲያስቀለብሱ መጣር ያስፈልጋል።

ለቀጣይም ለሀገሪቱ ስጋት የሚሆነው የባለሀብቱ ክፍል ነው። ይህ ክፍል በገንዘቡ ሁሉንም ማድረግ የሚችል ሲመሰለው ህግ አውጪ ፤ ህግ ተርጓሚና ህግ አስፈፃሚዎችን መናቅ ሲጀምር ይህ ለሀገር ህልውና አስጊ ይሆናል ማለት ነው። ሀገራትም በእንደዚህ አይነት ሁኔታ የህልውና ስጋት ውስጥ እንዳይገቡ አገልግሎት ሰጪ ተቋማትንና ባለሀብቱን መነጠል ታላቅ አማራጭ መሆኑን ይናገራሉ።

ይህን አማራጭ ለመጠቀም አንዱና ዋነኛ ዲጅታላይዜሽን ሲስተም ውስጥ በመግባት ሲሆን ሰዎች በአካል እንዳይገናኙ የሚያደርግ ሲስተም መዘርጋት ያስፈልጋል። እንደ ሀገራችን ያሉ ግጭት እዚህም እዛም ለሚነሳባቸው ሀገራት ደግሞ ለግጭቶቹ መንስኤዎች አፋጣኝ ምላሽ በመስጠት ዳግም እንዳይቀሰቀስም ከሰሩ በማፅዳት ማስቆም ይገባል።

መምህር አቶ ሰለሞን መፍትሄ ይሆናል ያሉትን ሲናገሩ፤ ሀገሪቱ ውስጥ ያለው የፖለቲካ ንግድ ቆሞ የሀሳብ የበላይነት ካልመጣ የሀገሪቱን ህልውና አደጋ ውስጥ ይከታል። ማህበረሰቡ የሀሳብ ልእልናን ተቀብሎ ሰው በሀሳቡ አሳምኖ ወደ ስልጣን ከመጣ ሀሳቡንም ወደ ስራ የሚቀይር ካልሆነ በስተቀር አሁንም እንደ አፍጋኒስታን ፤ ሱማሌና የመሳሰሉት ሀገሪቱ አደጋ ውስጥ መግባቷ አይቀርም። መንግስት ተቋማዊ ምስረታ ሪፎርም በማድረግ ሀሳብ ገዥ የሚሆንበት ሰው ከማንነቱ በላይ እውቀቱ ወደ ስልጣን የሚመጣበት ሁኔታ ቢመቻች መልካም ይሆናል ይላሉ።

ምሁራኖቹ እንደሚሉት የፖለቲካ ገበያ መነሻው ሀገር ውስጥ የሚከሰት ሁከትና ብጥብጥ ነው። የገበያ ግርግር ለሌባ ያመቻል እንዲሉ ሀገር በአንድም በሌላም ምክንያት መረጋጋት ስታጣ ያልተገቡ አካሄዶች በርክተው ይታያሉ።

በአጠቃላይ ከምሁራኑ ሀሳብ እንደምንረዳው የፖለቲካ ገበያው ለሀሳብ የበላይነት ቅድሚያ መስጠት እንደሚገባው ነው። መንግስትም እንደ መንግስት ተቋማትን ከብልሹ አሰራር በማንጻት ከሙስና የፀዳ ማህበረሰብ፣ ሀሳብን የበላይነት የሚቀበል ዲሞክራሲያዊት ሀገር መገንባት ይገባዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

## ሴቶች ሶፍት ዌር ቴክኖሎጂ በማበልፀጉና በመጠቀሙ ጎዳና

ሰላማዊት ውቤ


ወጣት እየሩሳሌም ዘውዱ


ወይዘሮ እናንዬ ሁሴን


ወይዘሮ ዓለምፀሐይ በቀለ

እየሩሳሌም ዘውዱ ትባላለች። ብዙም በሴቶች ተመራጭ ያልሆነውንና ሴቶች ደፍረው የማይገቡበትን ሶፍት ዌር ኢንጂነሪንግ ነው ያጠናችው። አሁን ላይ የሥራ መስኳ አድርጋ እየሠራችበት ያለችውም ይሄንኑ ሶፍት ዌር ኢንጅነሪንግ ነው። "መስኩ ሴቶች በየትኛውም ቦታና ሁኔታ ላይ ሆነው መሥራት የሚችሉበት ነው። ጉልበት የሚጠይቅ ባለመሆኑም ሳይከብዳቸው በቀላሉ ይሠሩበታል" ትላለች ጠቀሜታውን ስታብራራ ።

እየሩሳሌም እንደምትለው ከገቢ አንፃርም ቢሆን በቴክኖሎጂው ሴቶች በሌላ መስክ ሠርተው ከሚያገኙት በብዙ እጥፍ የተሻለ ክፍያ ይገኝበታል። ከወንድ ጓደኞቻቸው ወይም ከትዳር አጋሮቻቸው ጥገኝነት ተላቅቀው ዳጎስ ያለ ደሞዝ በማግኘት በተመቻቸ ሁኔታ ራሳቸውን ሊያስተዳድሩበትም የሚያስችል ነው ። ሥራው በየትኛውም ቦታና ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ሊሠራ የሚችል በመሆኑ የዶላር ክፍያ የሚያስገኝበት ዕድል መኖሩ የሴቷን ገቢ የበለጠ ላቅ ያለ እንዲሆን ያደርግላታል። እንደ ዓለምም ሆነ እንደ አገር ቴክኖሎጂው በደረስንበት ዘመን በእጅጉ ተፈላጊ መሆኑንና ለኢትዮጵያም አስፈላጊ መሆኑን ወጣት እየሩሳሌም ታነሳለች። ይሄ አሁን ላይ ከወንዶች በበለጠ ሁኔታ ሥራ አጥ ለሆኑት ሴቶች መልካም አጋጣሚ ነው። ምክንያቱም ቴክኖሎጂው በአገር ውስጥም ሆነ በውጭው ዓለም በእጅጉ ተፈላጊ ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ በስፋት እንዲሠማሩና እንዲጠቀሙ ያደርጋቸዋል።

ሆኖም እየሩሳሌም እንደምትናገረው በሀገራችን በተለይም ቀደም ባሉት ዓመታት ብዙ ሴቶች ወደ ሶፍት ዌር ኢንጂነሪንግ ቴክኖሎጂ ሙያ መስክ ደፍረው የሚገቡበት ሁኔታ አልተለመደም ነበር። እሷም ብትሆን ወደ ከፍተኛ ትምህርት ስትገባ ሶፍት ዌር ኢንጅነሪንግ አጠናለሁ የሚል ዕቅድ አልነበራትም። ሆኖም መስክ መረጣ ሳይገባ በመጀመሪያው ሴሚስተር በጨበጠችው የአጠቃላይ ኢንጂነሪንግ ዕውቀት በኋላ ሀገሪቱ ምን ሊያስፈልጋት እንደሚችል፤ዘመኑ የቴክኖሎጂ መሆኑን፤ ብዙ ሴቶች የሌሉበት ግን ለሴቶች በጣም ጠቃሚ መሆኑንና እሷ እዚህ ላይ ብትሠራ ስኬታማ እንደምትሆን ተረድታ ነው የመረጠችው። ደግሞም እንደ ግንባታና ሌሎች ሙያዎችም ጉልበት የማይጠይቅ ቀላል መሆኑ እንድትመርጠው አነሳስቷታል። ‹‹ስለሶፍት ዌር ኢንጂነሪንግ ስንማር ወደድኩት። ምን ምን እንደያዘም መገንዘብ ቻልኩ›› ስትልም በዋናነት ይሄንኑ መስክ በመምረጥ ለመማር መወሰኗን ደጋግማ ትገልፃለች። እናም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የከፍተኛ ትምህርቷን ስትከታተል ሶፍት ዌር ኢንጂነሪንግን እሷን ጨምሮ ጥቂት ቀድሞ ስለ ቴክኖሎጂው ዕውቀቱ ያልነበራቸው ሴቶች ብቻ በነዚህ መስፈርቶች ለማጥናት መረጡት። ‹‹ለኛ ለሴቶች ግን አብዛኛው የቴክኖሎጂው ትምህርት አዲስ ነበር›› ብትልም በሴት ተማሪዎች በኩል ያለው አቀባበል ከጊዜ ወደ ጊዜ በጣም እየተሻሻለ መምጣቱን ታነሳለች። ከዓመት ወደ ዓመት ሽግግር ሲደረግም በትምህርት አቀባበል በኩል ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል እየሆኑ መምጣታቸውን ታወሳለች። እንደምታስታውሰው በርካታ ወንዶች ነበሩ ለማጥናት የመረጡት። ግን ወንዶች ቴክኖሎጂውን ሊመርጡ የቻሉበት እውነታ ከሴቶች በእጅጉ ይለይ ነበር። ገና ከጅምሩ እንደተረዳችው ወንዶች ከቴክኖሎጂው ጋር የቀደመ ትውውቅ ነበራቸው።

በመሆኑም ሆን ብለውና እሱን ለመምረጥ አስበው ነው ወደ ዩኒቨርሲቲ የገቡት። እሱን መምረጥ የተሻለ ገቢ እንደሚያስገኝና በሥራ ዓለም ለመሠማራት አስቻይ ሁኔታዎች እንደነበሩትም አሳምረው ያውቁ ነበር። ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ ቴክኖሎጂውን በሚገባ ያውቁት እንደነበርም በኩራት ሲናገሩ የማድመጥ ዕድሉን አግኝታለች። ‹‹ምክንያቱም እነሱ ከመጀመሪያ ደረጃ ጀምሮ የፈለጉትን ለማድረግ የሚችሉበት ሰፊ ዕድል አላቸው። በቤት ውስጥ እንደ ሴቷ የሥራ ጫና የለባቸውም። የቤተሰብ ክልከላም ሳይመለከታቸው ነው የሚያድጉት። ሴቷ ስትሆን በአብዛኞቹ ወላጆች የምትሠራው ሁሉ ክትትል ሊደረግባት ይችላል። እንደ ሶፍት ዌር ያሉት ቴክኖሎጂዎች ላይ ትኩረት ብታደርግ እንደ ሥራ ፈት ወይም እንደባለጌ ልትቆጠርና ላይፈቀድላት ይችላል። ወንዶች ግን ከዚህ ሁሉ ተፅዕኖ ነፃ ናቸው። ከቴክኖሎጂው ጋር የቀደመ ትውውቅ ለማድረግ የረዳቸውም ይህ ነው። በዚህ የተነሳ እሷ ወደ ዩኒቨርሲቲ ገብታ ቴክኖሎጂውን በመረጠችበት ዘመን ወንዶች በብዛት መርጠውት እንደነበር በክፍል ቆይታዋ ታዝባለች። የመረጡት ፈልገውት ነው። ልምምድ ሲያደርጉበት ስለቆዩና በትምህርቱ የጠለቀ ዕውቀት ስለነበራቸው ነው ባይ ናት።

እንዲህም ሆኖ ምን አልባት እንበለጣለን የሚል ስጋት ይሁን ስለማይችሉ ውጤታማ አይሆኑበትም የሚልና ሌላ ምክንያት ኖሯቸው ባይገባትም አንዳንድ ወንዶች ተማሪዎችና መምህራን ጭምር ሴቶች ቴክኖሎጂውን ሊመርጡት ይገባል የሚል ዕምነት አልነበራቸውም። በግልፅ አነጋገር እንዲመርጡት የሚያበረታቱ በፍፁም አልነበሩበትም።

እንዲህም ሆኖ እሷን ጨምሮ ቴክኖሎጂውን የመረጡት የተወሰኑ ሴቶች ከወንዶቹ ተማሪዎች ጋር እራሳቸውን በዕውቀቱ ለማመጣጠን ያደርጉት የነበረው ፉክክር ቀላል አልነበረም። ሴቶች አይችሉትም የሚለውን ጨምሮ ውጤታማ እንዳይሆኑ ይደረጉ የነበሩ ተፅዕኖዎች ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን በዩኒቨርሲቲው የነበራቸውን ቆይታ አክብዶባቸዋል ።

በርግጥ አንዳንድ መምህራን በደንብ ሴት ተማሪዎችን የሚያበረታቱበት ሁኔታ ነበር ፤ጠንክረው እንዲማሩ፤ ከወንዶች እኩል እንዲሠሩና ብቃት እንዲኖራቸው በእጅጉም ይደግፉሉ። ነገር ግን በቆይታዋ ከዚህ በተቃራኒው የሆኑ መምህራኖችም እንደነበሩም እየሩሳሌም ትጠቅሳለች። እንደ እሷ እነዚህ ዓይነቶቹ መምህራን ሴት ተማሪዎች በቴክኖሎጂው ዕውቀት አላቸው ብለው አያስቡም።

ምክንያቱ ደግሞ አንድ ፕሮጀክት ሰጥተዋቸው ሠርተው ሲያቀርቡ ቡድናቸው ውስጥ ወንዶች ካስገቡ ያን ፕሮጀክት በውጤታማነት የሠሩት ወንዶች እንጂ ሴቶች እንዳልሆኑ ያስባሉ። በግልጽም ሴቶች ሳይሆኑ ወንዶች ናቸው የሠሩት ሲሉ ይደመጣሉ። ለሴቶች ድካም ዋጋ አይሰጡም። በፍፁምም ሴቶች የሚሠሩ የማይመስላቸው አስተማሪዎች ነበሩ።

‹‹ደክመን ለፍተን የሠራነውን ፕሮጀክት በቡድናችን ውስጥ ወንድ በመቀላቀላችን እናንተ አልሠራችሁትም ያለን መምህርም ገጥሞን ነበር›› ስትልም ቅሬታ አዘል ትዝብቷን ትገልፃለች። የትኛውም ዓይነት ብቃት የሌለው ወንድ በቡድኑ ውስጥ ቢኖርና ከነሱ ይልቅ እሱ በሴቶቹ ድጋፍ በመደገፉ ብቻ የችሎታው ማነስ ቢሸፈንለት ፕሮጀክቱ በውጤታማነት ተሠርቷል ተብሎ የሚታመነው በዚህ ዓይነቱ ደካማ ወንድ ተማሪ መሆኑ ሲያማርራቸው ቆይቷል። እንዲህ ዓይነቱን ሴቶች አይችሉም የሚል የአንዳንድ መምህራኖቻቸውና የአብዛኞቹ ወንድ ተማሪዎች ጭፍን አመለካከት እነሱ በዘዴ ተቋቁመው ማለፋቸውንም ታወሳለች።

ሴቶች በሶፍት ዌር ኢንጅነሪንግ ቴክኖሎጂ ያለንን ብቃት ለመምህራኖቻችን ለማሳየትና የሰጡንን ፕሮጀክት እራሳችን በራሳችን መሥራታችንን እንዲያውቁ ቡድናችንን ሴት ብቻ እናደርግ ነበር›› ትላለች። እሷ እንደምትለው በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው በቴክኖሎጂው ሴቶች ብቃት የላቸውም የሚለው አሉታዊ ተፅዕኖ ተቋቁመው በመስኩ ውጤታማ ለመሆን ሲሠሩ ነው የቆዩት። በመጨረሻም ውጤታማ በመሆን በጥሩ ውጤት ትምህርታቸውን ለማጠናቀቅ በቅተዋል።

ከነዚህ መካከል በቴክኖሎጂው መስክ የተሻለ ዕውቀት ለመቅሰም የሚያስችል የትምህርት ዕድል በማግኘት ኦሮሚያ ጎዳና የተሰኘችው የክፍል ጓደኛዋ ኔዘርላንድ እንዲሁም ቱንጋ ተሰማ የተባለችው ጓደኛዋ ደግሞ ሩዋንዳ መሄዳቸውን ነግራናለች። በተለይ እሷ ከዩኒቨርስቲው ትምህርቷን በጥሩ ውጤት አጠናቅቃ በፈረንጆቹ በ2020 መመረቋንም ታወሳለች ።

‹‹እንዴውም በሶፍት ዌር ኢንጅነሪንግ መስክ በቂ ዕውቀት ስላለኝ በሥራ የተሠማራሁት ከመመረቄ በፊት ነው ›› ብላናለችም እየሩሳሌም። እንደነገረችን ከመመረቃቸው በፊት ለልምምድ Vintage technologies የተሰኘ ካንፓኒ ይወጣሉ። ካንፓኒው እሷና ሌሎች ሴት ጓደኞቿ በሶፍት ዌር ቴክኖሎጂ ብቃት እንዳላቸው ፈጥኖ ነው የተገነዘበው። በመሆኑም ለልምምድ የሚሰጥ ሥራ ሳይሆን ውጭ የሚወጡ ሥራዎችን ይሰጣቸው ጀመር። በሙያው ገቢ ማግኘት የጀመረችው ከዚህ ጀምሮ ነበር። ተመርቃ እንደወጣች ልምምድ ታደርግበት የነበረው ይሄው ካንፓኒ የቅጥር ጥያቄ አቀረበላት። በሥራ ፍለጋ ያጠፋችው ጊዜ ሳይኖር ፈጥና በመቀላቀልም ዳጎስ ያለ ደሞዝ ተከፋይ ሆነች። ትንሽ እንደሠራች አሁን ላይ እየሠራችበት ያለው JSI inc. የተሰኘ ካንፓኒ ባወጣው ማስታወቂያ ተወዳድራ በማሸነፍ ቀድሞ ትሠራበት ከነበረው በእጅጉ በተሻለ ደሞዝ ለመቀጠር በቃች። አሁን በምታገኘው በሌሎች የሙያ መስኮች ተሰማርቶ ከሚገኘው በእጅጉ የተሻለና ዳጎስ ያለ በጥሩ ሁኔታ ራሷንና ቤተሰቧን እያስተዳደረች በዚሁ ገንዘብ ነው።

አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ጀሞ አካባቢ የምትኖረው ወጣት እየሩሳሌም በኮቪድ 19 ምክንያት አንድ ሴሚስተር ዘግይታ ብትመረቅም ያጠናችው ሙያ ሥራ አስፈትቶ እቤት ውስጥ የሚያስቀምጥ ባለመሆኑ በቤቷ ውስጥ ተቀምጣ ስትሠራ ቆይታለች። አንዱ ቴክኖሎጂው ለሴቶች የሚሰጠው ጥቅም ቤት ውስጥም ሆነ በየትኛውም ሥፍራ ሊሠሩት የሚችሉት መሆኑ። በተለይ በወሊድ ጊዜ ልጆቻቸውን እያጠቡና እየተንከባከቡ ይተገብሩታል። ሴቶች በይበልጥ ቢሠሩበት የሚፈለገውምና የሚመረጠውም ለዚህ ነው።

እየሩሳሌም ይሄን ታሳቢ አድርጋም በግሏ በርካታ ሴቶች ቴክኖሎጂውን ምርጫቸው እንዲያደርጉ እየተጋች ትገኛለች። ትጋቷ ዕውቀቷን በተለይ ለጾታ አጋሮቿ በማካፈል የታጀበ ነው። ሴቶች ከፕሮግራሚንግ ጀምሮ ሌሎች የቴክኖሎጂው ዕውቀቶች እንዲኖራቸው በቅጥር በተሠማራችበት የሥራ መስክ ብቻ ሳይሆን በግሏም ነፃ ስልጠና በመስጠት ታግዛቸዋለች። የቴክኖሎጂውን መስክ ቢመርጡትም በተሻለ ሁኔታ ጠቃሚ ሊሆኑ እንደሚችሉ ሳታሰልስ ግንዛቤ ታስጨብጣለች። ሆኖም ሥራው በኢንተርኔት እንደመሠራቱ በማንኛውም ሁኔታ የሚከሰት የኤሌክትሪክ ኃይል ችግር እንደሚያስተጓጉለውና በዚህ በኩል እንደ ሀገር መፍትሔ መፈለግ እንደሚገባ ታሳስባለች።

ወጣቷ እንዳወጋችን በቴክኖሎጂው ዳጎስ ያለ ገቢ ከምታገኝበትና ከዋና እና ሴቶችን የሙያው ባለቤት ለማድረግ በግሏ ጭምር ከምትሮጥበት ሥራ በተጓዳኝ ከሌሎች የዕድሜ አቻዎቿ ጋር በመቀናጀት በቴክኖሎጂ ሥራ ለሀገሯም አስተዋፅዖ አድርጋለች። ይሄውም ‹‹የበጎ ፈቃድ አገልግሎት አስተዳደር የመረጃ ቋት›› በመሰኘት የበለፀገ ሶፍት ዌር ነው። አሁን ላይ ወደ አገልግሎት የገባው ይሄ ቋት የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ሰጪና አገልግሎት ፈላጊን በመመዝገብ ከመስፈርቶቹ ጋር ሊስማማ የሚችል አገልግሎት ሰጪና ተቀባይን የሚያገናኝ ሲሆን በተለይ የመረጃ ተደራሽ በመሆን ረገድ ብዙ ችግሮች ያሉባቸውን ሴቶች የበለጠ እንደሚጠቅም ታወሳለች።

‹‹በጎ ፈቃድ ላይ ብሠራም ሥራው የሚገኝበትን ሥፍራ በቀላሉ ለመለየትና ለማወቅ ለብዙ ዓመታት በእጅጉ ስቸገር ቆይቻለሁ›› የሚሉት ወይዘሮ እናኑ ሁሴን ወጣቷ ከዕድሜ አቻዎቿ ጋር በመሆን የፈበረከችው ቴክኖሎጂ በእጅጉ እንደጠቀማቸው ያወሳሉ። እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ ‹‹ዳንዬ›› የተሰኘ የበጎ አድራጎት ድርጅት መሥርተው እየተንቀሳቀሱ የሚገኙት ወይዘሮ እናኑ ‹‹እኔ ተደራሽ ላደርጋቸው የምፈልጋቸውን ግን ደግሞ በመረጃ እጦት ምክንያት ልደርሳቸው ያልቻልኳቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽ እንዳደርግ አስችሎኛልም›› ይላሉ። ሴቶች በቴክኖሎጂው መሳተፋቸው የበለጠ ሴቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ ማስቻሉን ያስገነዘባቸው መሆኑን ያስረዳሉ ።

የ‹‹ቤተ ሳይዳ›› በጎ አድራጎት ድርጅት መሥራችና ሥራ አስኪያጅ የሆኑት ወይዘሮ ዓለምፀሐይ በቀለም የወይዘሮ እናኑን ሀሳብ ይጋራሉ። በተለይ ሴቶች በማኅበረሰቡ ካለባቸው የተለያየ ተፅዕኖ አንፃር ለእንዲህ ዓይነቱ ሶፍት ዌር የማበልፀግ ቴክኖሎጂ ሙያ መቅረብ ሳይችሉ ቀርተው መኖራቸውን ያወሳሉ። በዚህም እራሳቸውንም ሆነ ሌሎች ሴቶችን መጥቀም ሳይችሉ ቀርተዋል። ብዙ ሴት ወጣቶች አሁን ድረስ በማኅበረሰቡ ውስጥ በተለይም በወንዶች ዘንድ ባለ ሴቶችን ከቴክኖሎጂው የማራቅ አስተሳሰብ ተፅዕኖ አሁንም ወደ ሙያው መግባት የሚፈሩ በርካታ ሴቶች መኖራቸውንም በተለያየ አጋጣሚ መታዘባቸውን ይናገራሉ። ወጣቷ እየሩሳሌም ደፍራና የቴክኖሎጂው ለሀገርና ለወገን በተለይም ለሴቶች ያለውን ጥቅም ተረድታ ወደ ቴክኖሎጂው በመቅረቧና አመለካከቱን በተግባር በመስበሯ እሳቸው የሚፈልጉትን መረጃ ማግኘት ማስቻሏንም በማሳያነት ያነሳሉ። በተለይ ቴክኖሎጂው ሴቶች በማኅበረሰብ ውስጥና በተፈጥሮ ልጅ መውለድና መንከባከብ እንዲሁም ካሉባቸው ከሌሎች ኃላፊነቶች አንፃር ቤት ውስጥና የተለያየ አካባቢ ሆኖ መሥራት የሚያስችላቸው መሆኑ ፋይዳውን ያጎላዋል። ዳጎስ ያለ ገቢ ለማግኘት የሚያስችል መሆኑም ራሳቸውን ያለማንም እርዳታ እንዲያስተዳድሩና የተሻለ ሕይወት እንዲኖሩ ያስችላል ብለውናል። እኛም ሀሳባቸውን ሁሉም ከዘመኑ ቴክኖሎጂ ጋር መለወጥና መሻሻል ብሎም ሀገራቸውን ማራመድ የሚፈልጉ ዜጎች እንዲገዙት በመመኘት ጽሑፋችንን ደመደምን ።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

የዛሬው የአዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን ከ54 ዓመት በፊት የታተሙ ጋዜጦች ይዘው የወጡትን ዘገባ ያስታውሰናል፡፡ ማኅበራዊ፣ ወንጀል ነክና እንስሳት ሕክምና ላይ ያተኮሩ ዘገባዎችን ለትውስታ ያህል መርጠናል፡፡ የደብረ ዘይት የከብት ሕክምና ኢንስቲትዩት የተለያዩ የእንስሳት በሽታ መከላከያ መድኃኒት እየቀመመ ለእንስሳት ሕክምና በሥራ ላይ ማዋሉ ከመረጥናቸው ዘገባዎች ተጠቃሽ ነው፡፡

**ለ፯ ሚሊዮን እንስሳት የሚበቃ መድኃኒት ተቀምሟል**

ደብረ ዘይት፤(ኢ.ዜ.አ.)፤ ደብረ ዘይት የሚገኘው የከብት ሕክምና ኢንስቲትዩት ፤በዚህ ዓመት ለ፯ ሚሊዮን ፬፻፴፫ሺህ ፫፻፺፫ እንስሳት የሚበቃ ልዩ ልዩ የእንስሶች በሽታ መከላከያ የሚሆን መድኃኒት መቀመሙን አንድ የኢንስቲትዩቱ ቃል አቀባይ ገለጠ፡፡

ቃል አቀባዩ ከዚህ አያይዞ እንዳስረዳው ፤የተቀመመው መድኃኒት ፫ ሚሊየን፫፻፴፰ ሺህ ፪፻ ዶዝ ለቀንድ ከብቶች፣ ለአሳማዎች በሽታ መከላከያ መሆኑን ገልጧል፡፡

እንደዚሁም፤ በተለይ የተዘጋጀ ፓስቴውሪላ ፩፻፸፯ ሺህ ፬፻፳፫ ዶዝ ፤አባ ጎርባ ለተባለው በሽታ መከላከያ፤ ፩፻፸፩ ሺህ ፪፻፶ ዶዝ፣ ለአባ ሠንጋ በሽታ መከላከያ ፬ሺህ ዶዝ፣ ፋውል ታይፎይድ ማለት(የዶሮ በሽታ) ፫ሺህ ፫፻ ዶዝ፣ ፋውል ኮሌራ (የዶሮ) በሽታ መከላከያ የሆኑ መድኃኒቶችን ቀምሞ በሥራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡

ቃል አቀባዩ አቶ ጌታሁን አበጀ ከዚህም በማያያዝ ፤ኢንስቲትዩቱ ባለፉት አራት ዓመታት በርካታ መድኃኒቶችን ቀምሞ በየጠቅላይ ግዛቶቹ ታድለው በሥራ ላይ መዋላቸውን ከገለጡ በኋላ ፤ የመከላከያ መድኃኒቱን ከውጭ ሀገር ስናስመጣ እዚሁ ስለሚቀመምና ስለሚዘጋጅ የከብት ሕክምና ዋና መምሪያ በሽታውን ለመከላከልም ሆነ፤ ፈጽሞ ለማስወገድ በየቦታው ያሠማራቸው ሠራተኞቹ መከላከያ መድኃኒት የማነስም ሆነ የማጣት ችግር አይገጥማቸውም ፡፡

የመከላከያ መድኃኒቶቹን በላቦራቶሪ ውስጥ ቀምመው የሚያዘጋጁ አንድ ኢትዮጵያዊ ዶክተርና ሦስት የውጭ አገር ዶክተሮች ይገኛሉ፡፡ ከዚህም ሌላ በቂ ትምህርት ያላቸው ቴክኒሺያኖችና የዶክተሮቹ ረዳቶች መኖራቸውን ገልጠዋል፡፡

**(ነሐሴ 11ቀን 1960 ከወጣው አዲስ ዘመን)**

**በሬ የሰረቀው ፩ ዓመት እሥራት ተቀጣ**

አሰላ (ኢ.ዜ.አ)፤ በቀለ ቶልቻ የተባለው ሰው በተከሰሰበት የስርቆት ወንጀል በ፩ ዓመት እሥራት እንዲቀጣ የጭላሎ አውራጃ ፍርድ ቤት ግንቦት ፳፩ ቀን በዋለው ችሎት ፈረደ፡፡

ተከሳሹ ግንቦት ፲ ፪ ቀን የአቶ ጌታሁን ወልደማርያምን ሁለት በሬዎች ሰርቆ ሲነዳ ከነኤግዚቢቱ ተይዞ ተከስሶ ፍርድ ቤት ከቀረበ በኋላ ፤አድራጐቱን ራሱ ከማመኑም በላይ በሕግ ምስክሮች ተረጋግጦበታል፡ ፡ስለዚህ ተከሳሹ በፈጸመው ወንጀል በ፩ ዓመት እሥራት እንዲቀጣ ሲበየንበት በእጁ የተገኙትም በሬዎች ለባለንብረቱ እንዲመለሱ ተወስኗል፡፡

በቀለ ቶልቻ ይህንን ወንጀል የፈጸመው ፤ በአሩሲ ጠቅላይ ግዛት በጭላሎ አውራጃ በደራ ወረዳ መሆኑን ዐቃቤ ሕጉ አቶ ለገሠ መንግሥቱ ገለጡ፡፡

እንዲሁም በዚሁ አውራጃ ግዛት በኮፈሌ ወረዳ ሙዳ ሔይሳ የተባለ ሰው በፈጸመው የሥርቆት ወንጀል በ፩ ዓመት እስራት እንዲቀጣ የጭላሎ አውራጃ ፍርድ ቤት ግንቦት ፳፪ ቀን የፈረደበት መሆኑን ሕግ አስከባሪው በተጨማሪ ገለጡ፡፡

(ሐምሌ 10 ቀን 1960 ከወጣው አዲስ ዘመን)

**የድርሰት ማኅበር ሽልማቱን ሲሰጥ ነው**

አዲስ አበባ፡(ኢ.ዜ.አ.)፤የኢትዮጵያ ድርሰት ማኅበር ካወዳደረ በኋላ ፤አሸናፊ ለሆኑ አምስት ሰዎች ሽልማት እንደሚሰጥ ተገለጠ፡፡ ማኅበሩ ከልዩ ልዩ ደራሲያን የቀረቡለትን ፺፩ የግጥም ድርሰቶች በታወቁ የሥነጽሑፍ ሰዎች ዳኝነት አስመርምሮ ፹፱ የሚሆኑት የውድድሩ ተካፋይ ከሆኑ በኋላ ፤ለመጨረሻ ውጤት አምስት የድርሰት ባለቤቶች አሸናፊዎች በመሆናቸው የተዘጋጀውን ሽልማት እንደሚያገኙ የድርሰት ማኅበር የሥራ አስኪያጅ ኮሚቴ አስታወቀ፡፡

የማኅበሩ ምክትል ሊቀመንበሩ አቶ አበራ ጀምበሬ እንደገለጡት ፤የድርሰቱ ውድድር ውጤት በተስተካከለ ዳኝነትና በምሥጢር የተጠበቀ ከመሆኑም በላይ ፤በጥንቃቄ የተመረመረ በመሆኑ ሽልማቱ በመጀመሪያ ደረጃ የተመሠረተ ነው ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ ድርሰት ማኅበር የአሁኑን ሽልማት የሚሰጠው ወደፊት የተሻለ ድርሰት ለማግኘት፤ ደራሲያንን ለማብቃትና የሥነጽሑፍን ቅርስና የቅኔን ውበት ለተከታዩ ትውልድ ለማቆየት ሲሆን ማኅበሩ ወደፊት የተሻሉ ጽሑፎችን በመጠበቅ ላይ መሆኑን ምክትል ሊቀመንበሩ በተጨማሪ ገልጠዋል፡፡

(ሐምሌ 10 ቀን 1960 ከወጣው አዲስ ዘመን)

**በጉርሱም አውራጃ የዝኖን መንጋ ጉዳት ማድረሱ ተገለጠ**

ጅጅጋ ፤(ኢ.ዜ.አ.)፤ በሐረርጌ ጠቅላይ ግዛት የጅጅጋና የጉርሱም አውራጃ ግዛቶችን በሚያዋስነው ሰሰም ጉብድሌይ በተባለው ቀበሌ የዝኖን መንጋ ጉዳት ማድረሱ ተገለጠ፡፡

ኰሎኔል ይልማ ተሾመ የአሥረኛ ብርጌድ ዋና አዛዥና የሰሜን ክፍለ ግዛት የበላይ አስተዳዳሪ ፊታውራሪ በሽር ሼክ አብዲ የጅጅጋ አውራጃ ገዢ እና ኰሎኔል ማሞ አስፋው የሰሜን ክፍለ ግዛት ፖሊስ ዋና አዛዥ ትናንት ወደዚሁ ሥፍራ ሔደው ሁኔታውን ተመልክተዋል፡፡

ባለሥልጣኖቹ እንደገመቱት የዝኖኑ መንጋ በአካባቢው ሕዝብ አዝመራ ላይ ያደረሰው ጉዳት ጐልቶ ባይታይም ፤ለወደፊት በስምጥ ሸለቆ ውስጥ ባለው ሰብል ላይ ሕዝቡ ተገቢውን የሆነ ጥበቃ ካላደረገ ጉዳት እንደሚያደርስ ገምተዋል፡፡

እንዲሁም ባለሥልጣኖቹ በጅጅጋ አውራጃ ግዛት በተለይ የዝኖኑ መንጋ ወደሚገኝበት ወደ ጐላ አጀ ተጉዘው በዚያም የዝኖኑ መንጋ በሰብል ላይ ያረሰውን ጉዳት በመመልከት ለወደፊት መፍትሔ በሚሆኑ ጉዳዮች ላይ ተነጋግረዋል፡፡

**(ነሐሴ 11ቀን 1960 ከወጣው አዲስ ዘመን)**

# ዓለም አቀፍ



## በዲሞክራቲክ ኮንጎ በቤተ ክርስቲያን ላይ በተፈጸመ ጥቃት 10 ሰዎች ተገደሉ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ዲሞክራቲክ ኮንጎ ውስጥ በሰንበት የጸሎት ሥነ-ሥርዓት ላይ በነበሩ ሰዎች ላይ በተፈጸመ የቦንብ ትቃት 10 ሰዎች ሲገደሉ 39 ደግሞ ቆስለዋል።

የአገሪቱ መንግሥት ካሲንዲ ተብሎ በሚጠራው እና በምሥራቃዊ የኮንጎ ክፍል ውስጥ በሚገኘው ቤተክርስቲያን ላይ የተፈጸመውን የቦንብ ጥቃት ከአይ ኤስ ጋር ግንኙነት ያለውን ቡድን አድርሶታል ሲል ወንጅሏል።

በጥቃቱ በቤተክርስቲያኑ የዕሁድ ጸሎትን ሲታደሙ የነበሩ 10 ሰዎች እንደተገደሉ ባለሥልጠናት አስታውቀዋል።

ከሟቾች በተጨማሪ 39 ሰዎች ለጉዳት የተዳረጉበትን ይህንን ጥቃት የአገሪቱ ወታደራዊ ተቋም "የሽብር ድርጊት" ነው ሲል የፈረጀው ሲሆን፤ ፈጻሚው 'አላይድ ዲሞክራቲክ ፎርስስ' ወይም 'ኤዲኤፍ' ነው ሲል ከሷል።

የተጠቀሰው ቡድን በምሥራቃዊ ዲሞክራቲክ ኮንጎ ውስጥ ሰፊ እንቅስቃሴ የሚያደርግ የአማጺ ቡድን መሆኑን ቢቢሲ ዘግቧል።

የኮንጎ መንግሥት ባወጣው መግለጫ በ'ኤዲኤፍ' የተፈጸመ ነው ያለውን የቦምብ ጥቃት "አጥብቆ ያወግዛል።"

በመግለጫው መንግሥት "በእዚህ አስቀያሚ የሽበር ጥቃት" ቤተሰቦቻቸውን ላጡ ሰዎች የተሰማውን "ጥልቅ ሐዘን" ገልጿል።

በዲሞክራቲክ ኮንጎ የተሰማራው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ተልዕኮ በካሲንዲ የተፈጸመውን "አስነዋሪ" ያለውን ጥቃት አውግዟል።

"ይህ የሽብር ጥቃት በዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ሠራዊት በተለያዩ የጦር ግንባሮች ሽንፈት በደረሰበት ኤዲኤፍ እንደተፈጸመ ግልጽ ነው" ሲል የአገሪቱ መንግሥት ቃል አቀባይ አንቶኒ ሙላሻይ ገልጸዋል።

ቃል አቀባዩ ጨምረውም ለጥቃቱ መደበኛ ያልሆነ ቦንብ ጥቅም ላይ መዋሉንም ተናግረዋል።

ካሲንዲ የኤዲኤፍ እንቅስቃሴ ጠንክሮ ከሚታይበት ቢኒ ከተባለ አካባቢ የ8 ኪሎ ሜትር ርቀት ያለው ነው።

ባለፈው ወር የሀገሪቱ የተመድ ተወካይ በጸጥታው ምክር ቤት ቀርበው የጸጥታ ችግር ከዲአር ኮንጎ ዋነኛ ፈተናዎች መካከል አንዱ ነው።

በአውሮፓውያኑ 1990ዎቹ ብቅ ያለው ኤዲኤፍ የተፈጠረው በኡጋንዳ በተፈጠረ ውስጣዊ ቅሬታ የተፈጠረ ነው።

ሆኖም በዲአር ኮንጎ እንደአዲስ መታየት ከጀመረ በኋላ በኮንጎ ተከታታይ ጥቃት እየፈጸመ አለምአቀፋዊ የጀሃዲስቶች ገጽታ እየያዘ ይገኛል።



ማቴዎ ማሲኒ ዲናሮ

## ለ30 ዓመታት ሲፈለግ የነበረው የጣሊያን ማፊያ ቡድን መሪ ክሊኒክ ውስጥ ተያዘ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ለሦስት አስርት ዓመታት ሲታደን የቆየው የጣሊያን ተፈላጊ የማፊያዎች አለቃ ማቴዎ ማሲኒ ዲናሮ ሲሲሊ ውስጥ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ዋለ።

በጣም የሚፈራው ኮሳ ኖስትራ የማፊያ ቡድን አለቃ እንደሆነ የሚታመነው ማቴዎ ማሲኒ ዲናሮ የተያዘው በጣሊያኗ ግዛት ሲሲሊ ዋና ከተማ ውስጥ በሚገኝ አንድ የግል ክሊኒክ ውስጥ እንደሆነ ተዘግቧል።

ከተከሰሰባቸው ወንጀሎች መካከልም በ1992 (እአአ) ፀረ ማፊያ ዐቃቢያነ ሕግ የነበሩትን የጂዮቫኒ ፋልኮኔ እና የፓውሎ ቦርሴሊኖ ግድያዎች ይጠቀሳሉ።

በተጨማሪም በ1993 ሚላን፣ ፍሎረንስ እና ሮም ውስጥ የሰው ነፍስ ባጠፉ የቦንብ ጥቃቶች እና ከማፊያ ቡድን አፈንግጦ ምስክር የሆነ ግለሰብ የ11 ዓመት ልጅ ላይ ለተፈጸመ አፈና፣ ማሰቃየት እና ግድያ ይገኙበታል።

ማቴዎ ማሲኒ ዲናሮ በኮሳ ኖስትራ ቡድኑ አማካይነት ሕገወጥ ገንዘብን ሕጋዊ ማድረግ እና የዕጽ ዝውውርን ጨምሮ በርካታ ከባድ ወንጀሎችን በበላይነት በመምራት አስፈጽሟል ተብሎ ይታመናል።


ምንም እንኳን ማቴዎ ማሲኒ ዲናሮ ከ1993 (እአአ) ጀምሮ ከፖሊስ ተደብቆ የቆየ ቢሆንም፣ ካልታወቀ ቦታ ሆኖ ትዕዛዝ በመስጠት እስካሁንም ድረስ ተከታዮቹ ሲመራ እንደቆየ ይታመናል።

የግለሰቡን መያዝ ተከትሎ የጣሊያኗ ጠቅላይ ሚኒስትር ጂዮርጂያ ሜሎኒ "የማፊያ የወንጀል ቡድን ዋነኛ አባል" የሆነውን በቁጥጥር ስር በማዋላቸው የአገሪቱን ጦር ሠራዊት አመስግነው "ይህም ለአገሪቱ ታላቅ ድል ነው" ሲሉ ተናግረዋል።

የጣሊያን መገናኛ ብዙኃን እንደዘገቡት ለሰላሳ ዓመታት ሲፈለግ የነበረው ግለሰብ በክሊኒኩ ውስጥ ህክምና ሲደረግለት በነበረበት ጊዜ በፖሊስ ተይዞ ወደ አንድ ምስጢራዊ ስፍራ ተወስዷል።

ማቴዎ ማሲኒ ዲናሮ ቀደም ሲል ከበርካታ የግድያ ወንጀሎች ጋር በተያያዘ በሌለበት ክስ ተመስርቶበት የእድሜ ልክ እስራት ተፈርዶበታል ሲል ሮይተርስ አስነብቧል።

# ስፖርት



## ደራርቱ ቱሉ ዳግም የምስራቅ አፍሪካ ዞን አትሌቲክስ ምክትል ፕሬዘዳንት ሆና ተመረጠች

አስማየሁ ግዛው

የምስራቅ አፍሪካ ሃገራት የአትሌቲክስ ምክር ቤት የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ከትላንት በስቲያ በስካይላይት ሆቴል ባካሄደው ጠቅላላ ጉበዔ መርጧል። በጉባኤው የምክር ቤቱ ፕሬዘዳንት፣ምክትል ፕሬዘዳንትና ዋና ጸሐፊም መርጧል፡፡

የምስራቅ አፍሪካ ሃገራት አትሌቲክስ ሪጅን(ዞን5) አስር ሃገራትን ያቀፈ ሲሆን፣ ምክር ቤቱን የሚመሩ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትም በየአራት ዓመቱ በሚካሄድ ጉባዔ ይመረጣሉ። የዘንድሮው የምክር ቤቱ ጉባኤ በኢትዮጵያ አስተናጋጅነት የተካሄደ ሲሆን፣ ኢትዮጵያ፣ ሱዳን፣ ደቡብ ሱዳን፣ ኤርትራ፣ ጅቡቲ፣ ሶማሊያ፣ ዩጋንዳ፣ ታንዛኒያ፣ ኬንያና ሩዋንዳ ተሳትፈዋል። በጉባኤው የዞኑን የአትሌቲክስ እንቅስቃሴ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ አነስተኛ ኮሚቴም ተቋቁሟል። በጉባዔው የዞኑን አትሌቲክስ ምክር ቤት ባለፉቱ አራት ዓመታት ሲመሩ የነበሩትን ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ዳግም ለመምረጥና በሌሎች ጉዳዮች ዙርያ መክሯል። በዚህም የዞኑን አትሌቲክስ ለቀጣይ አራት አመታት የሚመሩት ፕሬዘዳንት፣ምክትል ፕሬዘዳንትና ዋና ጸሐፊ ተመርጠው ይፋ ተደርጓል። የዞኑን አትሌቲክስ በፕሬዘዳንትነት ለመምራት የኬንያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዘዳንት የሆኑት ጀነራል ጃክሰን ተዊን በድግሜ ሲመረጡ፤ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዘዳንት ረዳት ኮሚሽነር ጄነራል ደራርቱ ቱሉ ምክትል ፕሬዘዳንት ሆና በድጋሜ ተመርጣለች። ሳዲቅ ኢብራሂም ከሱዳን



በዋና ጸሐፊነት መመረጣቸውም ታውቋል።

የአትሌቲክስ ዞኑ ምክር ቤት በጉባኤው የተለያዩ አጀንደዎችን በማንሳት የተወያየና አቅጣጫዎችን ያስቀመጠ ሲሆን፣ ከነዚህም ውስጥ ምስራቅ አፍሪካ የአትሌቲክስ እምቅ ሃብት ያለበት አካባቢ እንደመሆኑ ተገቢው ትኩረት እንዳልተሰጠው ተነስታል። በዓለም አትሌቲክስም በቂት ኩረትና ውክልናን እዲያገኝ አዲሱ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እንዲሰራ አቅጣጫ ተቀምጧል። ሌላው የስብሰባው ዋነኛ አጀንደ የነበረው የአበረታች ቅመሞች ተጠቃሚነት ጉዳይ ሲሆን፣ የምስራቅ አፍሪካ አትሌቲክስ የህልውና ጉዳይ መሆኑንና አበረታች ቅመሞችን ለመቆጣጠር ጠንካራ ስራ መስራት እንደሚገባ አጽኖት ተሰጥቶታል። በሁሉም የዞኑ አባል ሃገራት ውድድሮች እንዲደረጉና አዘጋጅ ሃገር ትራንስፖርትን ጨምሮ ለመስተንግዶ አስፈላጊውን ነገር ማሟላት እንዳለበትም ተወስኗዋል። ጉባኤው በቀጣይም በየአባል ሃገራት እንደሚደረግ ተነግራል።

በጉበኤው እስከ አሁን እየተሰሩ ያሉ ስራዎች እንዴት እየተሰሩ እንዳሉ ግምገማና ወደፊት አትሌቲክሱን እንዴት እናሰድገው የሚሉት ሃሳቦች ውይይት ተደርጎባቸው አቅጣጫ እንደተሰጠባቸውም ታውቋል።

የዞኑ ምክር ቤት በጉባኤው በመጪዎቹ አራት አመታት ምን ስራ እንደሚሰራ፣እንዴት እንደሚሰራና እንዴት በቅንጅትና መግባባት ስኬታማ እንደሚሆንም ምክረሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

በጉባኤው አፍሪካ አትሌቲክስ ኮንፌዴሬሽን ፕሬዘዳንት ሃመድ ካልካባ በክብር እንግድነት የተገኙ ሲሆን፣ ጉባኤው በሁሉም የኮንፌዴሬሽኑ አባል ዞኖች ተደርጎ ከተጠናቀቀ በኋላ የአፍሪካ አትሌቲክስ ኮንፌዴሬሽን ጉባኤ በመጪው ሚያዝያ የሚደረግ ይሆናል። ይህም ጉባኤው እ.አ.አ ሚያዝያ 23/2023 በዛምቢያ ሉሳካ የሚካሄድ ሲሆን በዚህ ጉባኤ የኮምፌዴሬሽኑ ፕሬዘዳንት ይመረጣል ተብሎ ይጠበቃል። ለዚህም የምስራቅ አፍሪካ አትሌቲክስ ዞን ድጋፉን ለሃመድ ካልካባ ለመስጠት ቃል ገብተል። ፕሬዘዳንት ሃማድ ካልካባ በበኩላቸው ዞኑ ለሚሰጣቸው ድጋፍ አመስግነው ድጋሚ ከተመረጡ በዞኑ ያለውን የአትሌቲክስ አቅም በደንብ ለመጠቀም እንደሚሰሩ ቃል ገብተዋል። በተጨማሪም ፕሬዘዳንቱ አፍሪካ በዓለም አትሌቲክስ በቂ ተወካይ እንዲኖራትም ጥረት እንደሚያደርጉ አክለዋል። ፕሬዘዳንቱ «እንደ አትሌትና እንደ ስፖርት ማህበረሰብ ሰላምን መደገፍ አለበን፣ ሰላም ከሌለ ስፖርት አይኖርመም» ሲሉም ተናግረዋል።

የአትዮጵያ አትሌቲክሰ ፌዴሬሽን ፕሬዘዳንትና የዞኑ አትሌቲክስ ምክትል ፕሬዘዳንት ረዳት ኮሚሽነር ጄነራል ደራረቱ ቱሉ በበኩሏ፣ በአለም ደረጃ የምስራቅ አፍሪካ አትሌቶች በውጤት ረገድ የበላይነቱን የሚይዙ ቢሆንም እንደ አገልግሎታቸውና ውጤታቸው በአለም ደረጃ የሚገባቸውን ቦታ አግኝተዋል ተብሎ እንደማይታመን ተናግራለች። ደራርቱ አያይዛም እንደ ምስራቅ አፍሪካና እንደ አጠቃላይ እንደ አፍሪካም ጭምር በአለም አቀፍ አትሌቲክስ ቦታ ማግኘት እንደሚያስፈልግና የሚወጡ ህጎችም ላይ መወያየት እንደሚያስፈልግ አስረድታለች። በአሁኑ ወቅት አፍሪካ በአለም አቀፍ አትሌቲክስ ውስጥ ሶስት ተወካይ እንዳላትና ይህን ቢያንስ ወደ ስድስት ለማሳደግ መስራት አንደሚገባም ገልፃለች። በምስራቅ አፍሪካም የተሻለ አትሌቲክስንና የተሻለ ውጤታማ አትሌቶችን ለማፍራትም ጥረት እንደሚደረግ አክላለች። በተጨማሪም ሁሉም ፌዴሬሽኖች በማዘወተሪያ ቦታዎች መስፋፋት ላይ መስራት አንደሚገባ ስራ አስፈፃሚው በውይይቱ ማሳቱን ደራርቱ አብራርታለች።

የምስራቅ አፍሪካን አትሌቲክስ በጣም እያሰጋ ያለው አበረታች ቅመም(ዶፒንግ) በመሆኑ ይህን ችግር ለመቆጠጠር በርካታ ስራ እንደሚሰራ የተናገረችው ደራርቱ፣ በመጨረሻም ለሃገራችን ሰላም ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባዋል ስትል መልዕክቷን አጋርታለች፡፡

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ የፌ/ጠ/ዐቃቤ ህግ እና በተከሳሽ ወ/ሮ ሐሊማ ሰይድ አደም መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 12ኛ ወንጀል ችሎት ባለው በህገወጥ መንገድ የውጭ ምንዛሬ ይዞ መገኘት ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ በ15/05/2015 ዓ.ም. በ3፡30 ሰዓት ላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡ ተከሳሽ በቀጣይ ቀጠሮ ባይቀርቡ በሌሉበት እንደሚሰጥ ፍርድ ቤቱ አዟል፡፡

**በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 12ኛ ወንጀል ችሎት**

### ማስታወቂያ

የባለንብረት ስም አቦነህ መንግስቱ ልጎታ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A64412 የተሸከርካሪዉ አይነት አነስተኛ አውቶቡስ (ከ12 ያነሰ መቀመጫ) የሻሲ ቁጥር J11VLH61V00047913 ሞዴል LH61LV-QRBW የሊብሬ ቁጥር 027233 የሞተር ቁጥር 2L-1339301 ከላይ የተጠቀሰው የተሸከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 3/5/2015 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይገዌዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

### የኦዲት አገልግሎት ጨረታ ማስታወቂያ

የሐምብራ ቢዝነስ ግሩፕ አክሲዮን ማህበር በ ሪል እስቴት ዘርፍ ተሰማርቶ የሚሰራ ድርጅት ሲሆን ደርጅቱ ከ2015 እስከ 2017 በጀት ዓመት (ለ 3 ዓመት) ሂሳብ በውጭ ኦዲተር ለማስመርመር የውጭ ኦዲተሮችን በጨረታ አወዳድሮ የሂሳብ ስራ ኦዲት ማድረግ ይፈልጋል፡፡ በመሆኑም በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ በዘርፉ የንግድ ፈቃድ የቫት ተመዝጋቢ ቲን (TIN) ያላቸውና የዘመኑን ግብር ለመክፈላቸው እንዲሁም ከገቢዎች ሚ/ር ክሊራንስ ማቅረብ የሚችሉ ከኢትዮጵያ ሒሳብ አያያዝና ኦዲት ቦርድ(Certificate of Competency from accounting & auditing board of Ethiopia)እውቅና ያለው የምስክር ወረቀት እና IFRS(International Financial Reporting Standards) ትግበራ ላይ የተሞከሮ ወይም የልምድ ሰነድ እንዲሁም የቴክኒካል እና የፋይናንስ ፕሮፖዛል ቅጂ ማቅረብ የሚችሉ ተጫራቾች ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ባሉት 5(አምስት) ተከታታይ ቀናት ውስጥ ተጫራቾች የሚጫረቱበትን ዋጋ እና የጨረታ ማስረከቢያ መረጃዎችን በስም በታሸ ኤንቨሎፕ ማቅረብ ይችላሉ።

አድራሻችን፡- ፒያሳ ሱማሌ ተራ ተክለሀይማኖት ሆስፒታል ፊት ለፊት ግሎባል ኢንሹራንስ ህንፃ 2ተኛ ፎቅ ዋና መ/ቤት ቢሮ ቁጥር 49 ይገኛል።

ስልክ 011 8547211/09 44 30 73 37/38፣ አዲስ አበባ

**የሐምብራ ቢዝነስ ግሩፕ አክሲዮን ማህበር**

## ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም ፈሪድ ሙሪድ የሰሌዳ ቁጥር 1-19176 ኦሮ የሊብሬ ቁጥር 000379172 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በቀን 28/03/2015 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ሰሌዳውን ወድቆ፣ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የአዳማ ከተማ ትራንስፖርት ኤጀንሲ**

ከሳሽ የአቢሲኒያ ትራንስፖርት አክስዮን ኃ.የተ.ግ.ማህበር እና በተከሳሽ አቶ አራጌ ተበጀ መካካል ስላለው የፍታብሔር ክርክር አስመልክቶ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በእናንተ ላይ ክስ ስላቀረቡ እንድትቀርቡ ሆኖ ችሎት ላይ የማይቀርቡ ከሆነ ክርክሩ እናንተ በሌላችሁበት የሚካሄድ መሆኑን ተረድታችሁ በቀነ ቀጠሮ 19/05/15 ዓ.ም 4፡00 ሰዓት እንድትቀርቡ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አዟል።

**የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የፍታብሔር ችሎት**

የባለንብረቱ ጌታነህ አበራ ሰሌዳ ቁጥር 1-27814 ኦሮ ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ደብርት ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በቀን 12/4/2015 ዓ.ም አመልክተዋል። በዚሁ መሰረት የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ሊብሬ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይገዌዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን።

**የጅማ ከተማ ትራንስፖርት ባለስልጣን**

### ድሬዳዋ አስተዳደር

ከሳሽ ወ/ሮ ትግስት ሀ/ማሪያም እና በተከሳሽ ወ/ሮ ማርሸት ተረፈ ተሠማ መካከል ያለው የፍታብሔር ክስ ክርክር ጉዳይ በተመለከተ ተከሳሽ በአድራሻው ተፈልጋ ያልተገኘች በመሆኑ ማስታወቂያው ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ፍ/ቤቱ ሬጅስትራል ቢሮ በመቅረብ ክሱን ወስደው መልሶዎን ለጥር 12 ቀን 2015 ዓ.ም በጽሑፍ እንዲያቀርቡ እንዲሁም ክሱ ለመስማት ለጥር 16 ቀን 2015 ዓ.ም ጠዋት 3:00 የተቀጠረ በመሆኑ በእለቱ እንዲቀርቡ በተባለው ጊዜ ባይቀርቡ ጉዳዩ በሌሉበት የሚታይ መሆኑ የድሬዳዋ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ድሬዳዋ ምድብ 1ኛ ፍትሐብሔር ችሎት አዟል።

**የድሬዳዋ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

### የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ

በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክ/ከ ወረዳ 02 ቀበሌ 02 የቤት ቁጥር 806 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0003027067 ፖስፊክ ሊንክ ኢትዮጵያ ሪል ስቴት ሀ/የተ/የግ/ማህበር ከተመዘገብኩበት ሰሜን ምዕራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት ደረሰኝ ውስጥ የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) የዱቤ ደረሰኝ ያልተሰራበት ከቁጥር 001 እስከ 0500፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) የእጅ በእጅ ደረሰኝ ያልተሰራበት ከቁጥር 001እስከ 0500፣ የ ገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ የተሰራበት ከቁጥር 01 እስከ 075 እና ያልተሰራበት ከቁጥር 076 እስከ 01000 እና ዊዝሆልዲንግ ደረሰኝ ያልተሰራበት ከቁጥር 014 እስከ 01250 የጠፋ ሰለሆነ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል። ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀስው በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ሰሜን ምዕራብ አዲስ አበባ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ።

**ግብር ከፋይ ስም ፖስፊክ ሊንክ ኢትዮጵያ ሪል ስቴት ሀ/የተ/የግ/ማህበር**